# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2016 የስራ ዘመን አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

## ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ

## ነሐሴ 2016

## ዓዲግራት

## የይዘት ሰንጠረዥ (Table of Contents)


| ቁጥር | ይዘት | ገፅ |
|---|---|---|
| | አጠቃላይ መግቢያ | 2 |
| 1 | መደበኛ ስራ እንደገና ለመጀመር የተደረጉ የዝግጅት ስራዎችና አፈፃፀማቸው | 2 |
| 2 | ተማሪዎችን ስለመቀበልና የመማር ማስተማሩ ሂደት | 8 |
| 3 | የዩኒቨርሲቲው አይሲቲ መሰረተልማት እንደገና ስለማሰራትና ማደራጀት | 13 |
| | 3.1. የዴታ ሰንተር ስራዎች | 13 |
| | 3.2. ስማርት ክፍሎች እና የአይዲያሃብ ቴክኖሎጂ አገልግሎት | 14 |
| | 3.3. ቨርቹዋል ዴስክቶፕ ኢንፍራስትራክቸር | 14 |
| | 3.4. የኔትወርክ ዝርጋታ ስራዎች | 15 |
| | 3.5. የሲሲቲቪ ካሜራዎች ዝርጋታና መከታተያ ክፍል | 15 |
| | 3.6. ግቢ ሙሉ የሚያካልል የዋይፋይ አገልግሎት | 16 |
| 4 | የግንባታ ስራዎች በተመለከተ | 17 |
| 5 | የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች | 19 |
| 6 | በርካታ የተማሪዎች ፈተናዎች የተሰጡበት የትምህርት አመት | 23 |
| 7 | ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲና ዓዲግራት አጠቃላይ ሆስፒታል | 25 |
| 8 | በዩኒቨርሲቲው ስለሚገኙ ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች | 28 |
| 9 | የበጀት አጠቃቀም | 32 |
| 10 | አዲስ የስራ መዋቅር አፈፃፀም | 34 |
| 11 | ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች | 35 |
| | እዝል 1. ዩኒቨርሲቲው ከተመሰረተበት ጀምሮ እስከ ሰኔ 2016 ያስመረቃቸው ተማሪዎች መረጃ | 38 |
| | እዝል 2. በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት የሚከናወኑ መካከለኛ የምርምር ፕሮጀክቶች | 39 |

## አጠቃላይ መግቢያ

በጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ውድመትና ጉዳት የደረሰበት እና መደበኛ ስራውን እንዲያቆም ተገዶ የነበረው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ጥቅምት 2015 የተደረገው የፕሪቶርያ ሰላም ስምምነት ተከትሎ ተቋርጦ የነበረው መደበኛ ስራውን ለመጀመር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በመነጋገርና በመተባበር እንዲሁም ሁኔታው የፈቀደው ዝግጅት በማድረግ ሐምሌ 2015 መጨረሻ ላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ መደበኛ ስራውን እንደገና መጀመር ችሏል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ሶስተኛ ትውልድ ተብለው ይጠሩ ከነበሩት አስር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ በመሆን እና 960 ተማሪዎችን ለመጀመርያ ጊዜ በመቀበል በወጉ ስራውን የጀመረው ማክሰኞ ህዳር 26/2004 (Tuesday Dec. 5/2011) ነው። የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 (ቆየት ብሎ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 የተተካው) ለዩኒቨርሲቲው መቋቋም አጠቃላይ ህጋዊ መሰረት ያስቀመጠ ሲሆን በተለይም ደግሞ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን በተመለከተ ግንቦት 18/2003 በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003 "ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ" በሚል ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ሆኖ የተቋቋመ መንግስታዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ማስተማር፤ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን ናቸው። በአገሪቱ በተደረገው ዩኒቨርሲቲዎችን በተልእኮና በትኩረት የመለየት ስራ (Differentiation) መሰረት ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ሁሉን አቀፍ (Comprehensive) ተብለው ከሚጠሩት ዩኒቨርሲቲዎች ምድብ ውስጥ የሚገኝ ነው። የዩኒቨርሲቲው የ2016 የትምህርት አመት የአፈፃፀም ሪፖርት ወይም በአመቱ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ስራዎች የያዘ ዶኩመንት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 1. መደበኛ ስራ እንደገና ለመጀመር የተደረጉ የዝግጅት ስራዎችና አፈፃፀማቸው

ዩኒቨርሲቲው ከደረሰበት ውድመትና ጉዳት አንፃር መደበኛ ስራውን እንደገና ለመጀመር ለየት ያለ የዝግጅት ሰራ ማከናወን እንደሚገባ በማመን የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በተለይም ከታህሳስ 2015 ጀምሮ የተለያዩ ዝግጅቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። በዚሁም መሰረት ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከገንዘብ ሚኒስቴር ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል።

ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች በዋናነት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ስምምነት ተደርሷል፤

- ስራ ለመጀመር የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ፣
- ከመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ጋር ስራ ለመጀመር የሚያስችሉ ውይይቶች፣ ዝግጅቶች እና የስራ ስምሪቶችን ማከናወን፣
- የውድመትና ጉዳት ዳሰሳ መደረግ እንዳለበት ወይም ተደርጎ ከሆነ ደግሞ በሚገባ በሰነድ መልክ መዘጋጀት እንደሚገባ፣
- የደረሰው ውድመትና ጉዳት በሙሉ እስኪተካ ከመጠበቅ ይልቅ መሰረታዊ የሚባሉ ግዥዎችና ጥገናዎች በማከናወን ተማሪዎችን በተቻለ ፍጥነት መቀበል የተሻለ አማራጭ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲዎቹ ስራ በማቋረጣቸው ምክንያት ትምህርት ሳይማሩ በክልሉ ወይም በሌላ ቦታ የቆዩ ተማሪዎች፣ እንዲሁም በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ይማሩ የነበሩና በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት አቋርጠው በክልሉ ውስጥ የቆዩ ተማሪዎችን በመቀበል ትምህርት እንዲጀመር ማድረግ፤
- የ12 ክፍል ፈተና አልፈው በ2016 አዲስ የሚመደቡ ተማሪዎች ስለሚኖሩ እነሱንም ለመቀበል ዝግጅቶች መደረግ እንዳለባቸው እና የመቀበል አቅማቸውን ዩኒቨርሲቲዎች ማሳወቅ እንደሚኖርባቸው፣
- በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸው የነበሩ የዩኒቨርሲቲዎቹ መምህራን ዩኒቨርሲቲዎቹ ስራ ለመጀመር በሚዘጋጁበት ጊዜ አሁን ካሉበት ዩኒቨርሲቲዎች ወደ እናት ዩኒቨርሲቲያቸው እንዲመለሱ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ለሚመለከታቸው ዩኒቨርሲቲዎች ደብዳቤ እንደሚፃፍላቸው፣ እና
- የተለመደው የግዥ አሰራር በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ ስራ ለመጀመር አስቸጋሪ ስለሚሆን ከግዥና ንብረት ባለስልጣን ፈቃድ በመጠየቅ በልዩ ሁኔታ ግዥዎችን ማከናወን፤

ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በተደረገው መግባባት ደግሞ የሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የ2015 በጀት በተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀ ስለሆነ ዩኒቨሲቲዎቹ በተለይም መደበኛ በጀት ከወዲሁ መጠቀም እንደሚቻል አቅጣጫ ተሰጥቶበታል። ከ2013 መጨረሻ ወር ጀምሮ ለበርካታ ወራት ያልተከፈለ ውዝፍ የመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ደመወዝ አስመልክቶ ከታህሳስ ወር 2015 ጀምሮ በመጀመርያ የሶስት ወራት ለሁሉም ሰራተኞች እንዲከፈል፣ ቀጥሎ ደግሞ በየወሩ ክፍያ እንዲፈፀም አቅጣጫ የተሰጠበት ሲሆን ከታህሳስ 2015 በፊት ስላለው ውዝፍ ደመወዝ ግን በሌላ ጊዜ ሊታይ እንደሚችል ተቀምጧል። በዚህም መሰረት

እንዲፈፀም የተደረገ ሲሆን የ2014 ውዝፍ ደምወዝ ግን እልባት ባለመሰጠቱ ምክንያት እስከ 2016 በጀት አመት መጨረሻ ላይ ሊከፈል አልቻለም።

የግዥ ስራዎችን በተመለከተ ደግሞ ለግዥና ንብረት ባለስልጣን የሚከተሉትን ግዥዎች (በያንዳንዱ የግዥ ርእስ በዝርዝር የተቀመጡ የእቃዎች/ማቴርያሎች ይገኙበታል) በልዩ ሁኔታ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም ይፈቀድልን ዘንድ ጥያቄ አቅርበን፤

1. የፅህፈት መሳርያዎች (ስቴሽነሪ ማቴርያሎች)፣
2. የጥገና መሳርያዎችና ማሽኖች፣
3. የተማሪዎች ምግብ ቤት (ኪችን) እና የመኝታ ቤት (ዶርሚተሪ) እቃዎች
4. የኤሌክትሪክ ማቴርያሎች
5. የኤሌክትሪኒክስ እቃዎች
6. የህክምና መሳርያዎችና መድሃኒቶች
7. የላቦራቶሪ፣ የፅዳትና የንፅህና ማቴርያሎች
8. ፈርኒቸሮች
9. መስተዋቶች

ዩኒቨርሲቲው ስራውን እንደገና ለመጀመር እነዚህ ግዥዎች ያላቸውን ወሳኝ ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን በተራ ቁጥር 1፣ 3፣ 4፣ 7 እና 9 የተመለከቱት በዋጋ ማቅረቢያ፤ በተራ ቁጥር 2፣ 5፣ 6፣ እና 8 የተዘረዘሩትን ደግሞ በውሱን ጨረታ በልዩ ሁኔታ እንድንገዛ ፈቅዶልን በተፈቀደው መሰረት በርካታ ግዥዎችን አከናውነናል። የግዥና ንብረት ባለስልጣን ላደረገልን እገዛ ደግሞ ከፍተኛ ምስጋና ሊቸረው ይገባል። በባለስልጣኑ ድጋፍ ባይደረግልን ኖሮ ዩኒቨርሲቲው እንደገና ስራ ለመጀመር አይቻለውም ነበር።

ከላይ ከተጠቀሱት ግዥዎች በተጨማሪም ከባለስልጣኑ ፈቃድ በመጠየቅ እንዲሁም በተቀመጠው የግዥ አሰራር ስርአት ተጨማሪ ግዥዎች (ለምሳሌ የተማሪዎች የምግብ አቅርቦት በግልፅ ጨረታ እንዲገዛ ነው የተደረገው) አከናውነናል።

እንደአዲስ የተደራጀው የዩኒቨርሲቲው አስተዳድር ቦርድም ሰኔ 01/2015 የመጀመርያ ስብሰባውን በማድረግ በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጀው የ3 አመት (2016 — 2018) እና የቦርዱ የውስጥ መተዳደርያ ደንብ ተወያይቶ ያፀደቀ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው መደበኛ ስራውን በተቻለ ፍጥነት እንዲጀምር አቅጣጫ ሰጥቶበታል። አስተዳደር ቦርዱ በታሕሳስ ወር 2016 ደግሞ በዓዲግራት ከተማ በአካል በመገኘት ዩኒቨርሲቲው በወቅቱ ያለበት ሁኔታ ምልከታ

አካውኗል። በምልከታው ወቅት በዩኒቨርሲቲው የደረሰው ውድመት፣ የግንባታ ስራዎች (በዋናው ግቢ፣ በሁለተኛው ወይም ምውፃእ ወርቂ ግቢ፣ እንዲሁም በሶስትኛው የማስተማርያ ሆስፒታል ግቢ) ያሉበት ሁኔታ በዝርዝር ለማየት ችሏል። ምልከታውን ተከትሎ ከኮንስትራክሽን ባለስልጣን ከመጡት ሃላፊዎችና ባለሞያዎች፣ ከስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች፣ እና ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጋር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ሰፊ ውይይት ያደረገ ሲሆን ለመጪው ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ተግባራት አስመልክቶም የስራ መመርያ ሰጥቶበታል። ቦርዱ በወቅቱ መደበኛ ስብሰባውን ያከናወነ ሲሆን ታሕሳስ 06/2016 በተደረገው የተማሪዎች ምረቃ በአል በመገኘት የበአሉ ተካፋይ ሆኗል።

ተማሪዎችን ለመቀበል የተሰራው ሌላው ስኬታማ የዝግጅት ስራ የተማሪዎች ምግብ ቤት ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ለመጠገን የተሰራው ስራ ነው። ይህ ስኬታማ የጥገና ስራ የተከናወነው በግቢው ውስጥ በየቦታው ተጥለው የነበሩት የብረታብረትና የጣውላ ግብአቶችን በመጠቀም፣ መገዛት ያለባቸው ጣውላዎችና ሌሎች ግብአቶች፣ እንዲሁም ለጥገና አስፈላጊ የሆኑ ቀላል ማሽኖችን በመግዛት ሲሆን የጥገና ስራውን የሰሩት ደግሞ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ናቸው። መምህራኖቹ የኢንጂነሪንግ ኮሌጅ (ሜካኒካል ኢንጂነሪንት እና ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ) መምህራን ሲሆኑ ለስራው ተፈላጊ የሆኑ ማቴርያሎች ደግሞ ቀደም ብሎ በተገለፀው መሰረት ከግዥና ንብረት ባለስልጣን የተፈቀደልንን አሰራር በመጠቀም ነው። በዚሁም መሰረት ከ1500 በላይ የምግብ ቤት ወንበሮችና ከ500 በላይ የምግብ ጠረጴዛዎች በመምህራን በኩል እንዲጠገኑ ተደርገዋል። መምህራኑ ከወንበርና ጠረጴዛ ጥገና በተጨማሪ ሌሎች ጥገናዎችም (ለምሳሌ በሮች፣ የኤሌክትሪክ መስመሮችና መብራቶች፣ ወዘተ) አከናውነዋል።

ከዚሁ በተጨማሪም አስፈላጊ ክፍሎቻቸው ተነቅለው የተወሰዱ እና ከጥቅም ውጭ የሆኑ የወዳደቁ ዴስክቶፕ ኮምፕዩተሮችም ተፈላጊ እቃዎች እንዲገዙ በማድረግ በመምህራን እና የአይሲቲ ዳይሬክቶሬት ባለሞያዎች ተጠግነው ጥቅም ላይ ሊውሉ ችለዋል። ተጠግነው ጥቅም ላይ የዋሉት ኮምፕዩተሮች ከ400 በላይ ሲሆኑ እነዚህ ባይጠገኑ ኖሩ በአመቱ የተከናወኑ የተለያዩ የፈተና ስራዎች (የድህረ ምረቃ መግቢያ ፈተና ወይም GAT፣ የሬሜዲያል ፈተና፣ የተመራቂ ተማሪዎች መውጫ ፈተና ወይም Exit Exam፣ እንዲሁም የ12 ክፍል መልቀቂያ ፈተና) ማከናወን አይቻልም ነበር።

ይህ የጥገና ስራ የውስጥ ሃይልን በመጠቀም የቱን ያህል ውጤታማ ስራ ማከናወን እንደሚቻል በተግባር የታየበት ሲሆን በዚሁ ስራ ላይ የተሳተፉ መምህራን፣ የአይሲቲ

ዳይሬክቶሬት ባለሞያዎች፣ እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ክፍተኛ ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። እነዚህ የጥገና ስራዎች ባየከናወኑ ኖሮ ተማሪዎችን እንደአዲስ ለመቀበልም ይሁን የተለያዩ የፈተና አገልግሎቶች ማከናወን አይቻልም ነበር።

በዝግጅት ወቅት ሌላ ትኩረት የተሰጠው ስራ የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦት ጉዳይ ነው። የዩኒቨርሲቲው የውሃ አቅርቦት የሚመጣው በዋናነት ዩኒቨርሲቲው ከግቢው ውጭ ካስቆፈራቸው የውሃ ጉድጓዶች ነው። ከአብዛኛዎቹ ጉድጓዶች ወደ አንድ ቦታ የሚሰበሰቡበት የማከማቻ ማእከል (Collection Chamber) ስላለ ከዚሁ ማእከል ወደ ዩኒቨርሲቲው በትራንስፎርመር/በጀነሬተር እየተገፋ የሚገባ የውሃ አቅርቦት ነበር። ሆኖም በጦርነቱ ወቅት አብዛኛዎቹ ትራንስፎርመሮች/ጀነሬተሮች ስለተበላሹ ወይም ስለተቃጠሉ ከነዚህ ጉድጓዶች የሚገኝ የውሃ አቅርቦት ሊገኝ አልቻለም። ተማሪዎችን ለመቀበል እንደ አንድ አማራጭ የተወሰደው በግቢው ውስጥ ተቆፍሮ አገልግሎት ሳይሰጥ የነበረው የውሃ ጉድጓድ ተፈላጊ መሳሪያዎች እንዲገጠሙ በማድረግ እና የኤሌክትሪክ አቅርቦትም ከግቢው ውስጥ እንዲያገኝ በማድረግ ወደ ስራ ማስገባት ነበር። ይሄም በተሳካ ሁኔታ ተሰርቶ ከዚሁ ጉድጓድ የውሃ አቅርቦት ሊገኝ ችሏል። ከግቢው ውጭ ከሚገኝ አንድ ጉድጓድ ደግሞ ትራንስፎርመሩ ተቃጥሎ ሊሰራ ባይችልም ጀነሬተሩ ግን የተወሰነ የጥገና ስራ በማድረግ የውሃ አቅርቦት ሊሰጥ ችሏል። ከነዚህ ሁለት ጉድጓዶች ከሚገኘው ውሃ በተማሪዎች ምግብ ቤት አከባቢ አብዛኛው ጊዜ የ24 ሰኣት የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ተደርጓል። ከዚሁ በተጨማሪም የውሃ ቦቴን በመከራየት በግቢው ውስጥ በየቦታው ወደሚገኙ ሮቶዎች እንዲሞላ በማድረግ ተማሪዎች በአቅራቢያቸው የውሃ አቅርቦት እንዲያገኙም ተደርጓል። ሆኖም ግን የተቃጠሉ/የተበላሹ ትራንስፎርመሮች በበጀት አመቱ ሊጠገኑ ወይም ሊተኩ ባለመቻላቸው በ2017 የበጀት አመት ሊጠገኑ የሚችሉትን በመጠገን እና ሊተኩ የሚገባቸውን በግዥ በመተካት የተሻለ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል።

የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በተመለከተ ደግሞ በአንድ በኩል በግቢው ውስጥ ካሉት ትራንስፎርመሮች የተቃጠሉ ስለሚገኙበት በሌላ በኩል ደግሞ የተበጣጠሱ መስመሮች፣ የተሰረቁ (የተዘረፉ) ብሬከሮች እና የማይሰሩ አምፑሎች በብዛት ስለነበሩ እነዚህን የመጠገንና የማስተካከል ስራዎች በሰፊው መስራት ይጠይቅ ነበር። በዚሁም መሰረት መገዛት የሚገባቸውን ገመዶች፣ ብሬከሮች እና አምፑሎች እንዲገዙ በማድረግ ሰፊ የጥገና ስራ እንዲሰራ በማድረግ ነው የተማሪዎች ዶርሚተሪዎች የመብራት አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረገው። በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ የሚገኙ ትራንስፎርመሮች የመጠገን ወይም

የመተካት ስራ በበጀት አመቱ ሊከናወን ሰላልቻለ በ2017 ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሰራ ይሆናል።

የመኪና (የትራንስፖርት) አገልግሎትን አስመልክቶ ዩኒቨርሲቲው ከነበሩት 38 መኪኖች ውስጥ አብዛኛዎቹ የተበላሹ፣ የተዘረፉ ወይም የተወሰዱ በመሆናቸው የቀሩት መኪኖች በጣም ጥቂት ነው የነበሩት። ዩኒቨርሲቲው ከነበሩት ስድስት አውቶቡሶች ውስጥ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት ሁለት ብቻ ናቸው። የቢሮ መኪኖች ደግሞ ከአምስት የማይበልጡ ናቸው አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት። የተበላሹትን የማሰራት የተወሰዱትን የማስመለስ ስራ ከመስራት በተጨማሪ የኪራይ አውቶቡሶችን በመጠቀም የትራንስፖርት አገልግሎት የግድ ይል ስለነበር ሶስት አውቶቡሶችን ዩኒቨርሲቲው ተከራይቷል። ተወስደው የነበሩትን ለማስመለስ ጥረቶች ተደርጎ በርከት ያሉ መኪኖች እንዲመለሱ ተደርጓል። የተበላሹትን ደግሞ መጠገን አስፈላጊ ስለነበር በካምፓኒዎቻቸው እንዲጠገኑ አስተዳደር ካውንስሉ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት እንዲጠገኑ ተደርጓል። አንድ ፒክአፕ ያገለገለ መኪናም ከመንግስት ለዩኒቨርሲቲው የተሰጠ ሲሆን ይህም መኪና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ያለው የመኪና እጥረት በጣም ከፍተኛ ነው። ከጦርነቱ በፊት እያንዳንዱ ኮሌጅ የራሱ መኪና ተመድቦለት ይገለገል የነበረ ሲሆን አሁን ግን ኮሌጆች (ከግብርናና ጤና ሳይንስ በስተቀር) መኪና የላቸውም። በ2017 ይሄንን ከፍተኛ የመኪና እጥረት ለማቃለል ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

የፅዳት አገልግሎት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው ስራውን ቀደም ብሎ ወደ ውጭ እንዲወጣ (Outsource) አድርጎት የነበረ ሲሆን ይሄንን ስራ በመቀጠል ለ2016 በግልፅ ጨረታ አገልግሎቱ ባሸነፈው ድርጅት አመካኝነት እንዲገኝ ተደርጓል። የነበረው የጽዳት አገልግሎትም የሚመሰገን ነበር። ለ2017 ደግሞ በዚሁ የሚቀጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ የዝግጅት ስራው ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ አስፈላጊ ናቸው ተብለው በተለዩ ስራዎች ማለትም ከምግብ ቤት አገልግሎት ስራዎች ጋር የተያያዙ፣ ከተማሪዎች መኝታ ቤት አገልግሎት ጋር የተያያዙ፣ ከተማሪዎች ጤና አገልግሎት ጋር የተያያዙ፣ ከኤሌክትሪክ እና ውሃ አቅርቦት ጋር የተያያዙ፣ እንዲሁም የማስማርያ ግብአቶችና አቅርቦቶች ጋር የተያያዙ ስራዎችን በመለየትና ትኩረት በመስጠት የተከናወኑ ናቸው። የደረሰው ውድመትና ዩኒቨርሲቲው ያለበት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ ስራዎችን በመለየት (Identifying areas of priority) እነዚህ ስራዎች ላይ ርብርብ በማድረግ ነው ዩኒቨርሲቲው መደበኛ ስራውን እንደገና ሊጀምር የቻለው። እነዚህ

ስራዎችን ለማከናወን ደግሞ ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቦርድ ጀምሮ እስከ ትምህርት ክፍሎችና ሌሎች አስተዳደራዊ የስራ ክፍሎች በአትኩሮት የየድርሻቸውን እንዲወጡ በማድረግ ነበር እንዲከከናወኑ የተደረጉት።

በጦርነቱ ምክንያት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ (መምህራን፣ ሰራተኞች እና ተማሪዎች) ከፍተኛ የስነልቦና ጉዳት እንደደረሳቸው ለመገመቱ የሚያዳግት አይደለም። ዩኒቨርሲቲው ይሄንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በቂ ነው ባይባልም የግማሽ ቀን የትራውማ ሂሊንግ (Trauma Healing) ስልጠናበዩኒቨርሲቲው የስነልቦና ባለሞያዎች ለዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች በትምህርት ዘመኑ የመጀመርያ ወራት እንዲሰጥ ተደርጓል። ስልጠናው በሁለት ተከፍሎ የተሰጠ ሲሆን እያንዳንዱ ስልጠና ለግማሽ ቀን የተሰጠ ነው የነበረው። ስልጠናው በቂ ነው ባይባልም የአጋዥነት ጠቀሜታ እንደነበረው ግን የሚታመን ነው።

## 2. ተማሪዎችን ስለመቀበልና የመማር ማስተማሩ ሂደት

በጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ውድመትና ጉዳት የደረሰበት እና መደበኛ ስራውን እንዲያቆም ተገዶ የነበረው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ጥቅምት 2015 የተደረገው የፕሪቶርያ ሰላም ስምምነት ተከትሎ ተቋርጦ የነበረው መደበኛ ስራውን ለመጀመር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በመነጋገርና በመተባበር እንዲሁም ሁኔታው የፈቀደው ዝግጅት በማድረግ ሐምሌ 2015 መጨረሻ ላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ መደበኛ ስራውን እንደገና መጀመር ችሏል። ለ2016 የትምህርት ዘመን የተቀበልናቸው ተማሪዎች በአራት ምድብ የሚከፈሉ ናቸው። በአንደኛው ምድብ የሚመደቡት የዩኒቨርሲቲው መደበኛ ተማሪዎች ሆነው ዩኒቨርሲቲው መደበኛ ስራውን ሲያቆም ትምህርት አቋርጠው በዋናነት በትግራይ ውስጥ ያለትምህርት የቆዩ እና ዩኒቨርሲቲው ስራ ሲጀምር ትምህርት ካቆሙበት ለመቀጠል የተዘጋጁት ናቸው። በሁለተኛው ምድብ የሚመደቡት ደግሞ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ይማሩ የነበሩ ሆነው በጦርነቱ ምክንያት አቋርጠው ትግራይ ውስጥ የቆዩ እና በየዩኒቨርሲቲያቸው ትምህርት ያለፈባቸው የትግራይ ተወላጆች የሚያካትት ነው። በሶስተኛው ምድብ የሚመደቡት ደግሞ የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሆነው ዩኒቨርሲቲው በጦርነቱ ምክንያት ሲያቋርጥ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርት ሲቀጥሉ የቆዩ ሆነው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ሰራ ሲጀምር ተመልሰው (በሌላ ዩኒቨርሲቲ ከደረሱበት ደረጃ) የቀራቸውን ትምህርት በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ለመቀጠል የመጡትን የሚይዝ ነው። በአራተኛ ምድብ የሚመደቡት ተማሪዎች ደግሞ 2016

መጀመርያ ላይ የ12 ክፍል ፈተና ወስደው ያለፉትና ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡ አዲስ መደበኛ ተማሪዎችን የሚያካትት ነው። ከነዚህ ምድቦች በተጨማሪ የአስራ ሁለተኛ ፈተና ወስደው ያላለፉ ሆነው የማካካሻ ትምህርት (ሬሜዲያል) እንዲወስዱ ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡ (በአመቱ ሁለተኛ ሰሚስተር) የሬሜዲያል ተማሪዎችም የነበሩ ሲሆን ትምህርት ተከታትለው ፈተና እንዲወሰዱ ተደርገዋል።

ከላይ እንደተቀመጠው የተቀበልናቸው ተማሪዎች ሁኔታ ድብልቅልቅ ያለ መሆኑ መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም። ይሄንን የተደበላለቀ አይነት ስብጥር ያላቸውን ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተናገዱ በጣም ከፍተኛ ፈተና የበዛበት አመት እንደነበረ ማወቁ ተገቢ ይሆናል። በዚሁም ምክንያት የተማሪዎች ጥያቄዎች በጣም ብዙ ከመሆናቸውም በላይ ቅጥ ያጡ እና ለማስተናገድም አስቸጋሪ የነበሩበት ሁኔታ ነው የነበረው። ከተነሱት ጉዳዮች/ጥያቄዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት ባይቋረጥ ኖሮ ቀደም ብለው መመረቅ የነበረባቸው ተማሪዎች የማካካሻ ኮርስ እንዲሰጣቸው ያነሱት ጥያቄ፤
- ዩኒቨርሲቲው የተቀበላቸው ተማሪዎች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ በመሆናቸው እና ሲያቋርጡ የነበሩበት ደረጃ የተለያየ መሆኑ (ከፊሎቹ በአንደኛ ሰሚስተር ያቋረጡ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በሁለተኛ ሰሚስተር ያቋረጡ)፤
- ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተማሪዎች በመሆናቸው የቀሩዋቸው ኮርሶት የተለያዩ በመሆናቸው በበአንድ ወይም በሌላ ክፍል ውስጥ አንድ ላይ ለማስተናገድ አስቸጋሪ በመሆኑ ጥቂት ተማሪዎችም ቢሆኑ (አንድም ተማሪ ቢሆን) እድሉ ሊነፈጋቸው ስለማይገባ ተማሪዎቹን እንደየፍላጎታቸው ማስተናገዱ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮ የነበረ መሆኑ፤
- በአንድ ሰሚስተር ውስጥ የሁለት ሰሚስተር ተማሪዎች የተከሰቱ መሆናቸው እና ትምህርት ክፍሎች ኮርሶችን እና መምህራን በመመደብ በኩል ያጋጠማቸው ፈተና፤
- ሲንየር ተማሪዎችን የማካካሻ ኮርስ ለመስጠት ዩኒቨርሲቲው ስለወሰነላቸው (ማለትም በአንድ አመት ውስጥ ሶስት ሰሚስተር እንዲሰጣቸው ስለተደረገ) በአንድ በኩል መምህራን በአንድ አመት ውስጥ ሶስት ሰሚስተር ማስተማራችን ተገቢ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ማቅረባቸው (በዚሁም ምክንያት ከትርፍ ሰአት ክፍያ ተያይዞ ጥያቄ ያስነሳ ጉዳይ መሆኑ) በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ተማሪዎች በእድሉ እኛ ተጠቃሚ እንድሆን አልተደረግንም የሚል ጥያቄ ማቅረባቸው፤

- ከነሐሴ 2014 በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና (Exit Exam) መውሰድ እንዳለባቸው በትምህርት ሚኒስቴር የወጣ መመርያ የሚያስገድድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች እኛ በጦርነት ምክንያት ባናቋርጥ ኖሮ መመረቅ የነበረብን ቀደም ብሎ ስለነበረ የመውጫ ፈተና እኛን ስለማይመለከት መፈተን የለብንም የሚል በጣም ጠንካራ ጥያቄ የቀረበ መሆኑ አልፎ አልፎም የረብሻ የሚመስሉ ምልክቶች የታዩ መሆናቸው፤
- በጦርነቱ ጊዜ ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተዛውረው እንዲማሩ ከተፈቀደላቸው ተማሪዎች ውስጥ እኛ ጋር የወሰዱዋቸው ኮርሶች አስመልክቶ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ያላቸው ሪኮርድ እየታየ የተላከ ሳይሆን ራሳቸው ተማሪዎቹ ለተመደቡበት ዩኒቨርሲቲዎች በሰጡት የማረጋገጫ ፎርማ እንዲስተናገዱ የተደረገ ስለሆነ ይሄንን መሰረት በማድረግም በተመደቡበት ዩኒቨርሲቲ የቀራቸውን ኮርሶች ያጠናቀቁት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ጊዚያዊ ወረቀት (ማጠናቀቃቸው ተረጋግጦ ዋናው ዲግሪ በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በኩል እስኪሰጣቸው ድረስ) ተሰጥቷቸው ስራ እስከመያዝ የደረሱም ይገኙበታል። በመጨረሻም (ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በተደረሰው መግባባት መሰረት) በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የወሰዱዋቸው ኮርሶች ወደ ዩኒቨርሲቲያችን እንዲላክ ተደርጎ ስለማጠናቀቃቸው እየተረጋገጠ ነው ዲግሪው የሚፀድቅላቸው እና ሰርቲፊኬቱ የሚሰጣቸው። በዚሁም መሰረት እንዲሰራ ተደርጓል። ከነዚህ ውስጥ ግን የአንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲያችን ያጠናቀቁዋቸው ኮርሶች ሲጣራ የጎደሉዋቸው ኮርሶች እንዳሉ ለማወቅ ስለተቻለ ኮርሱን/ኮርሶቹን ካላጠናቀቁ ውጤት እንደማይሰጣቸው እንዲያውቁ ስለተደረገ ወደ ዩኒቨርሲቲው መጥተው ኮርሱን/ኮርሶቹን ማጠናቀቅ ችለዋል። ይህ በንዲህ እንዳለ የመውጫ ፈተኛ ደግሞ መውሰድ ሊጠበቅባቸው ሆነ። ተማሪዎቹ መውሰድ የለብንም ዩኒቨርሲቲው ደግሞ መውሰድ አለባችሁ በሚል የማያቋርጥ ሙግት የተገባበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከመውጫ ፈተና ጋር ተያይዞ ያጋጠመው ንትርክ አመቱን ሙሉ የዘለቀ እና እስካሁን እየቀጠለ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ከትምህርት ሚኒስቴር ጋርም ውይይት እየተደረገበት ይገኛል፤
- በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ሲማሩ ቆይተው በተሰጣቸው እድል ምክንያት እኛ ጋር ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የተደረጉ ተማሪዎች አስመልክቶ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በተደረሰው መግባባት መሰረት ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመረቁ የሚያስመርቃቸው ዩኒቨርሲቲ ከ50% በላይ ትምህርት በወሰዱበት ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ስምምነት ተደርሷል። በዚሁም መሰረት አብዛኛው ትምህርት እኛ ጋር

የወሰዱ ከሆነ ከሌላው ዩኒቨርሲቲ ውጤታቸው ወደኛ እንዲላክ ተደርጎ እንዲመረቁ ይደረጋል። አብዛኛው ኮርስ የወሰዱት በሌላ ዩኒቨርሲቲ ከሆነ ደግሞ ውጤታቸው ከኛ እንዲላክላቸው ተደርጎ በዛኛው ዩኒቨርሲቲ እንዲመረቁ ይደረጋል። በዚሁም መሰረት በሌላ ዩኒቨርሲቲ መመረቅ ያለባቸው ተማሪዎች ውጤታቸው ወደ ሌላው ዩኒቨርሲቲ እንድንልክ ደብዳቤ ተፅፎልን ውጤታቸውን ልከናል። ነገር አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ሊያስተናግዱዋቸው እንዳልቻሉ እስከ ትምህርት ሚኒስቴር የደረሰ ቅሬታ ቀርቦልናል፤

- ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች አንድ ወጥ የአካዳሚክ ካሌንደር አዘጋጅቶ ትምህርቱን ማካሄድ የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የተለያዩ ሁኔታዎችን ማስተናገድ ሊፈቅድ የሚችል አመላካች የአካዳሚክ ካላንደር እንዲዘጋጅ ነው የተደረገው።

ዩኒቨርሲቲው እነዚህ እና ሌሎች ጉዳዮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ቀደም ብሎ አስቦ የገባበት ነው የነበረው። በዚህም ምክንያት እንደተገመተው የትምህርት አመቱ በጣም አስቸጋሪ እና ተወዛዋዥ (turbulent) ሆኖ ነው ያለፈው። ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ያጋጠሙትን ችግሮች እየፈታ በሚገባ ለማስተናገድ ከፍተኛ ጥረት ያደረገበት እና ውጤታማ ስራ የተሰራበት አመትም ነው የነበረው።

በአመቱ የነበሩት የተማሪዎች ቁጥርም በአንድ በኩል አዲስ ተማሪዎች ዘግየት ብለው የተመደቡ በመሆናቸው፣ የረሜድያል ተማሪዎችም ወደ ዩኒቨርሲቲው የመጡት በሁለተኛ ሰሚስተር በመሆኑ፣ እንዲሁም ከታች እንደተቀመጠው በየጊዜው ተማሪዎች እየተመረቁ እንዲወጡ በመደረጉ በዩኒቨርሲቲው የነበረው የተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያየ ነው የነበረው። በግቢው የነበረው የተማሪዎች ብዛት እስከ 7000 ድረስ የደረሰበት ጊዜ የነበረ ቢሆንም በአመቱ መጨረሻ አከባቢ የነበሩት ተማሪዎች በዛት ግን (ቀደም ብለው የተመረቁትን ሳይጨምር) የሚከተለውን ይመስላል፤

- ቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች፤ ወንድ 2299፣ ሴት 1190፣ ድምር 3489
- ድህረ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች፣ ወንድ 108፣ ሴት 35፣ ድምር 143
- ሬሜድያል ተማሪዎች፤ ወንድ 429፣ ሴት 258፣ ድምር 687
- ጠቅላላ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት፤ ወንድ 2836፣ ሴት 1483፣ **ድምር 4319**

ከላይ ከተመለከተው የተማሪ ቁጥር በተጨማሪ ከክልሉ የትምህርት ቢሮ ጋር በተደረሰው ስምምነት መሰረት በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት አቋርጠው የነበሩ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የማጠናከርያ ትምህርት እንዲሰጣቸው በክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ትብብር ማድረግ ስለነበረባቸው 2400 የሚሆኑ የክልሉ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተና

ከመውሰዳቸው በፊት በዩኒቨርሲቲው ለሁለት ወራት (ነሐሴ 2015 እና መስከረም 2016) እንዲቆዩ ተደርጎ የማጠናከርያ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል።

የተማሪዎች ምረቃ በተመለከተ በአመቱ የዩኒቨርሲቲው ሰኔት አራት ጊዜ የተማሪዎችን ምረቃ አፅድቋል፤

1. ጥቅምት 23/2016
    - በድህረ ምረቃ (ወንድ 36፣ ሴት 9፣ ድምር 45)
    - በቅድመ ምረቃ (ወንድ 174፣ ሴት 104፣ ድምር 278)
    - ሁሉም ተመራቂዎች (ወንድ 210፣ ሴት 113፣ ድምር 323)
2. ታህሳስ 04/2016
    - በድህረ ምረቃ (ወንድ 46፣ ሴት 10፣ ድምር 56)
    - በቅድመ ምረቃ (ወንድ 1215፣ ሴት 568፣ ድምር 1783)
    - ሁሉም ተመራቂዎች (ወንድ 1261፣ ሴት 578፣ ድምር 1839)

ታህሳስ 06/2016 በደማቅ ሁኔታ የተከበረ የምረቃ በአል ተደርጎ ተማሪዎች እንዲመረቁ ተደርጓል። የምረቃው የክብር እንግዳ በመሆን ተማሪዎችን የመረቁልን የክልሉ የጊዚያዊ አስተዳደር ፕረዚደንት አቶ ጌታቸው ረዳ ሲሆኑ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ተሻለ በልሁ እንዲሁም የቦርዱ አባላት በበአሉ በመገኘት ለበአሉ ከፍተኛ ድምቀት ሰጥተውታል።

3. ሚያዝያ 02/2016
    - በድህረ ምረቃ (ወንድ 59፣ ሴት 11፣ ድምር 70)
    - በቅድመ ምረቃ (ወንድ 484፣ ሴት 423፣ ድምር 907)
    - ሁሉም ተመራቂዎች (ወንድ 543፣ ሴት 434፣ ድምር 977)
4. ሰኔ 26/2016
    - በድህረ ምረቃ (ወንድ 41፣ ሴት 11፣ ድምር 52)
    - በቅድመ ምረቃ (ወንድ 434፣ ሴት 126፣ ድምር 560)
    - ሁሉም ተመራቂዎች (ወንድ 475፣ ሴት 137፣ ድምር 612)

የአመቱ የማጠቃለያ የምረቃ ፕሮግራም ሐሙስ ሰኔ 27/2016 በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ የዋለ ሲሆን ተመራቂ ተማሪዎች በእለቱ በወጉ እንዲመረቁ ተደርጓል። የእለቱ የክብር እንግዳ በመሆነ ተማሪዎችን የመረቁልን ዶ/ር አልጋነሽ ተሰማ የክልሉ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ስራ ፈጠራ ካቢኔ ሰክሬታርያት ነው የነበሩ።

በድምሩ በአመቱ የተመረቁ ተማሪዎች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል፤

ሰንጠረዥ 1፤ የ2016 ተመራቂዎች ብዛት

| ተ.ቁ. | ተመራቂዎች | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ድህረ ምረቃ | 182 | 41 | 223 |
| 2 | ቅድመ ምረቃ | 2307 | 1221 | 3528 |
| ድምር | | 2489 | 1262 | 3751 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተቀመጠው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በአመቱ 3751 ተማሪዎችን አስመርቋል። ዩኒቨርሲቲው ስራውን ከጀመረበት ከህዳር 26/2004 ጀምሮ **አስር የተማሪዎች ምረቃ በአሎችን** ያከናወነ ሲሆን እስከ ሰኔ 2016 ድረስ ያስመረቃቸው ተማሪዎች ብዛት 25661 ደርሷል። በየአመቱ እና በየፕሮግራሙ የተመረቁ ተማሪዎች ዝርዝር መረጃ በእዝል 1 (በሪፖርት መጨረሻ ገፆች) ተመልክቷል።

## 3. የዩኒቨርሲቲው አይሲቲ መሰረተልማት እንደገና ስለማሰራትና ማደራጀት

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ከጦርነቱ በፊት ከሚታወቅባቸው ስራዎች አንዱ በኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (Information and Communication Technology, ICT) መሰረተልማት በሰራቸው ስራዎች ነበር። ይህ መሰረተ ልማት ግን በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። ዩኒቨርሲቲው እንደገና ስራውን ሲጀምር ሊሰራቸው ካቀዳቸው ስራዎች አንዱ የአይሲቲ መሰረተ ልማት ከጦርነቱ በፊት ከነበረበት ደረጃ በተሻለ እና ዘመናዊነትን በተላበሰ መልኩ አገልግሎት ሊሰጥ ወደሚችልበት ደረጃ ማድረስ ነው። በዚሁም መሰረት ከግዥና ንብረት ባለስልጣን ባገኘነው ፈቃድ መሰረት ትልቅ የአይሲቲ መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በመተግበር ላይ ነው። በዚህ ፕሮጀክት ስር በመከናወን ላይ የሚገኙ ዋና ዋና ስራዎች የሚከተሉት ናቸው፤

### 3.1. የዴታ ሰንተር (Data Center) ስራዎች

በዚህ ፕሮጀክት ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ ዳታ ሰንተሩን ማጠናከርና ማስፋፋት እንዲሁም ዳታ ሰንተሩን ለመከታተል የሚያስችል የኔትወርክ መከታተያ ማእከል (Network Operation Center, NOC) ማደራጀት የሚመለከት ነው። የዳታ ሰንተሩን ተጨማሪ መሳርያዎችን በመግጠም እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም አነስተኛ ዳታ ሰንተሮች (Mini Data Centers) አስፈላጊ ተብለው በተመረጡ ቦታዎች ላይ እንዲገጠሙ የሚደረግ ይሆናል። የዳታ ሰንተሩ የክትትል ማእከልም በተገቢው መልኩ ተደራጅቶ ለክክትልና ቁጥጥር ስራዎች በሚመች መልኩ የሚደራጅ ይሆናል። ዳታ ሰንተሩ

የማያቋርጥ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማግኘት ስለሚኖርበት በዋናው መስመር እና በጀነሬተር ከሚያገኘው የኤሌክትሪክ አቅርቦት በተጨማሪ የፀሃይ ሃይል (Solar Power) ምንጭ እንዲኖረው ይደረጋል። ለዚሁም የሚያስፈልጉ መሳርያዎች በአብዛኛው ገቢ የተደረጉ ሲሆን የመግጠም ስራውም በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል።

### 3.2. ስማርት መማርያ ክፍሎች (Smart Classrooms) እና የአይዲያሃብ (Ideahub) ቴክኖሎጂ አገልግሎት

የመማር ማስተማሩን ስራ በአዲስ ቴክኖሎጂ እየታገዘ እንዲከናወን ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከጊዜው ጋር ለመዘመንና ለመጓዝ ሊታለፍ የማይገባው ግብአት ነው። በዚሁም መሰረት በፕሮጀክቱ መሰረት ከሚሰሩት ሰራዎች ውስጥ የስማርት መማርያ ክፍሎች ይገኙበታል። በዚሁም መሰረት ሰባት ራሳቸውን የቻሉ ስማርት የመማርያ ክፍሎች (የድምፅ መሳርያዎች ጭምር የሚገጠሙላቸው) የሚደራጁ ይሆናል። ከዚሁም በተጨማሪ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት የሚሰጡ (Multipurpose) አገልግሎት የሚሰጥ (ለማስተማርያ እንደ ነጭ ሰሌዳ የሚያገለግል፣ እንዲቪድዮ ኮንፈረንስ የሚያገለግል፣ ከኢንተርኔት ጋር ተገናኝቶ የተለያዩ አገልግሎቶችን ሊሰጥ የሚችል፣ እንዲሁም ለፕረዘንቴሽን ስራዎች የሚያገለግል) የራሱ ካሜራና የድምፅ ስርአት ያለው አይዲያሃብ (IDEAHUB) የተባለ ቴክኖሎጂም እንዲገጠም ይደረጋል። በዚሁም መሰረት 14 አይዲያሃቦች ተገጥመው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረግ ይሆናል። እነዚህን በመጠቀም የትምህርት አሰጣጡ በአመቺ ቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ለመስጠት ያስችላል። በኦንላይን ለሚሰጡ ትምህርቶችም የራሱን የሆነ ድጋፍ ያደርጋል። ሁሉም ተማሪዎች የነዚህ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲሆን በተለይም የህክምና ተማሪዎች በሆስፒታል የሚደረጉ የቀዶ ህክምና ስራዎች (ከቅርብም ከሩቅም) ሊከታተሉ የሚችሉበት እድል ከፍተኛ ይሆናል። የነዚህ ቴክኖሎጂዎች የመግጠም ስራ የተጀመረ ሲሆን በ2017 የመጀመርያ ወራት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

### 3.3. ቨርቹዋል ዴስክቶፕ ኢንፍራስተራክቸር (Virtual Desktop Infrastructure, VDI)

ቪዲኢይ (VDI) ተብሎ የሚጠራው ቴክኖሎጂ ዴስክቶፕ ኮምፕዩተር የሚሰጠውን አገልግሎት በሙሉ የሚሰጥ ሲሆን የክምችት (Storage) እንዲሁም የላን (Local Area Network) እና የዋን (Wide Area Network) አገልግሎቶችን ከዋናው ዴታ ሰንተር (Data Center) ጋር ተሳስሮ (Networked ሆኖ) የሚሰራ መሆኑ ነው። እያንዳንዱ ተጠቃሚ (ተማሪዎችም፣ ሌሎች ተጠቃሚዎችም) የየራሳቸውን የመግቢያ ቃል (Password)

ተጠቅመው በዳታ ሰንተሩ በሚገኙ ሰርቨሮች የተመደበላቸውን የክምችት ቦታ (Storage area) ጋር እየገቡ ዶኩመንቶችን እና ሌሎች ጠቃሚ ፋይሎችን የሚያስቀምጡበትና የሚጠቀሙቸት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የላን እና የዋን አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ነው። የኢላይብረሪ (E-Library) እና የመስመር ላይ (Online) ትምህርቶችንና (E-Learning) አገልገሎቶችን ለማግኘት ይጠቅማል። ከዚሁም በተጨማሪ የተለያዩ የመስመር ላይ ፈተናዎች (Online Exams) ለማስተዳደር አይነተኛ መሳርያ ነው። በአይሲቲ መሰረተልማት ፕሮጀክቱ አመካኝነት 900 ቪዲአዮች (VDIs) የሚገጠሙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 700 አዲስ ሲሆኑ 200 ደግሞ ቀደም ብለው የነበሩና እንደአዲስ ተቀይረውና ተስተካክለው አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ቪዲአዮች ተተክለው ለአገልግሎት ዝግጁ በሚሆኑበት ወቅት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሙሉ በተለይም ለተማሪዎች በጣም ከፍተኛ የአይሲቲ አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናል። ዩኒቨርሲቲውም ሌሎች አገልግሎቶች (E-Library፣ E-Learning፣ Online Exams፣ eSHE፣ እና ሌሎች) ዘመናዊ በሆነ አግባብ ለመስጠት ያስችለዋል።

### 3.4. የኔትወርክ ዝርጋታ ስራዎች

የፕሮጀክቱ ሌላው ዋና ተግባር የኔትወርክ ዝርጋታ ስራዎችን ማከናወን ነው። በዚሁም መሰረት በግቢው ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከግቢው ውጭ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የመምህራን መኖርያ ኮንደሚንየሞች ከዳታ ሰንተሩ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ የኢንተርኔት አገልገሎት እንዲያገኙ የሚደረገው በተዘረጋው/በሚዘረጋው ኔትወርክ አመካኝነት ነው። ዝርጋታው ሲያልቅ መምህራን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ብቻ ሳይሆን በየቤታቸውም አስተማማኝ የሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ስለሚደረግ ለመማር ማስተማሩ ስራ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታመናል።

### 3.5. የሲሲቲቪ ካሜራዎች ዝርጋታ እና የመከታተያ ክፍል

የሲሲቲቪ (CCTV) ካሜራዎች መግጠም በአለም ላይ በስፋት እየተለመደ የመጣ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ የክትትልና የቁጥጥር ስራን ለማጠናከር የሚረዳ ቴክኖሎጂ ነው። በየቦታው የሚደረጉ ተገቢም ይሁኑ ተገቢነት የሌላቸው ተግባራትን ለመከታተል አይነተኛ መሳርያ ነው። በዚህ ፕሮጀክት አመካኝነት በርካታ ካሜራዎች ተፈላጊ ናቸው ተብለው በሚታመኑባቸው ቦታዎች የሚተከሉ ሲሆን እነዚህን ካሜራዎች በአንድ ቦታ ላይ ለመከታተል የሚያስችል የመከታተያ ክፍል የሚደራጅ ሲሆን በዚህ ክፍል አመካኝነት ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ለማከማቸት እና ለመከታተል የሚቻል ይሆናል። የተወሰኑ

ካሜራዎች የተተከሉ ሲሆን የመከታተያ ክፍሉም ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ቀሪ ስራዎች ደግሞ በ2017 የመጀመርያ ወራት የሚጠናቀቁ ይሆናል።

3.6. ግቢ ሙሉ የሚያካልል የዋይፋይ አገልግሎት (Campus Wide Wifi)

በሚዘረጉት የኔትወርክ መስመሮች በየቢሮውና በየክፍሉ የዋን እና የላን አገልግሎቶችን ማግኘት የሚቻል ሲሆን ግቢውን በሙሉ የሚያካልል የዋይፋይ አገልግሎት ደግሞ በዚህ ፕሮጀክት አመካኝነት የሚሰራ ይሆናል። ይህ አገልግሎት በዩኒቨርሲቲ ግቢ በሚገኝ ማንኛውም ቦታ የኔትወርክ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል ሲሆን ተፈላጊ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችም በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል።

ከአይሲቲ መሰረተ ልማት ስራዎች ጋር ተያይዞ በዓዲግራት ከተማ የሚገኙ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከዩኒቨርሲቲው ዳታ ሰንተር ጋር ተገናኝተው አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የፋይበር ዝርጋታ በኢትዮቴሌኮም አመካኝነት እየተደረገ ይገኛል። በከተማው የሚገኘው ሆስፒታልም ከዩኒቨርሲቲው ዳታ ሰንተር ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ለማገናኘት አስፈላጊ የዝርጋታ ስራዎች በኢትዮቴሌኮም አማካኝነት እንዲሰራ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው።

የተሻለ የአይሲቲ መሰረተ ልማት መኖር ሌሎችም ከፍተኛ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። እንደጥሩ ምሳሌ በዩኒቨርሲቲው መምህራን ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ከዋለ አመታትን ያሳለፈው የተማሪዎች ሪከርድ አስተዳደር ስርአት (Student Information Management System, SIMS) እንዲሁ ሌሎች ሊሰሩ የታሰቡ ሲስተሞች የበለጠ ስራ ላይ እንዲውሉ ጠቃሚ መሰረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል። አሁን በጥቅም ላይ ያለው የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርቲንግ ስርአት (IBEX) እንዲሁም 2017 ላይ ጥቅም ላይ ይውላል ተብሎ የሚታመንበት እና IFMIS ተብሎ የሚጠራው አዲስ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሪፖርቲንግ ስርአት (አዲሱ ሲስተም የሰው ሃብት እና የንብረት አያያዝ ስርአትን አጠቃሎ የተገበር ስርአት ነው) በመተግበር ላይ ባለው የአይሲቲ መሰረተ ልማት ፕሮጀክት አስተማማኝ እንዲገኝ ያደርጋል። በአገሪቱ እና በዩኒቨርሲቲያችን ከ2017 የበጀት አመት ጀምሮ የሚተገበረው eGP (Electronic Government Purchase) እየተባለ የሚጠራው የመስመር ላይ (Online) የግዥ ስርአት አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጥም በጣም አስፈላጊ መሰረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል።

## 4. የግንባታ ስራዎች በተመለከተ

በዩኒቨርሲቲው በርካታ የግንባታ ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኙ የነበረ ሲሆን በጦርነቱ ምክንያት ከጥቂቶቹ በስተቀር የግንባታ ስራዎች እንዲቋረጡ የተደረገበት ሁኔታ ነው ያለው።

በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ ያሉት የግንባታ ስራዎች ከታች በሰንጠረዥ 2 የተመለከቱት ናቸው። በ2016 የትምህርት ዘመን ከጥቂቶቹ በተለይም በተራ ቁጥር 13 እና 14 ከተቀመጡት በስተቀር የተደረገ የግንባታ ስራ አልነበረም ማለት ይቻላል። ዋናው ምክንያት ደግሞ በአንድ በኩል በጦርነቱ ምክንያት የደረሱ ዝርፊያዎችየነበሩ ቢሆንም ዋናው ምክንያት ግን ከከፍተኛ ዋጋ መጨመር ጋር ተያይዞ በነበረው ውል ለማስቀጠል አስቸጋሪ በመሆኑ እና ኮንትራክተሮች እና አማካሪዎች የዋጋ ጭማሪ እንዲደረግ በመጠየቃቸው ነው። ይሄንን ችግር ለመቅረፍ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደረ ቦርድ በተገኘበት ከኮንስትራክሽን ባለስልጣን ሃላፊዎች እና ባለሞያዎች እንዲሁም ከስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ጋር ታህሳስ 06/2016 ሰፊ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በዚሁ የምክክር ስብሰባ የአሰራር አቅጣጫዎች ተቀምጠውበታል። ከዚሁ በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ባለስልጣን ሃላፊዎች፣ ስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የተገኙበት ሁለተኛ የምክክር ስብሰባ በዩኒቨርሲቲው ግቢ የተደረገ ሲሆን ከተሳታፊዎች የተውጣጣ ኮሚቴ (በትግራይ ውስጥ የሚገኙ አራቱ ዩኒቨርሲቲዎችን ያካተተ) ተቋቁሞ ፕሮፖዛል እንዲያዘጋጅ ተደርጎ የአሰራር አቅጣጫ እንዲቀመጥበት ተደርጓል። በዚህም መሰረት በዋናነት በመንግስት የተቀመጠውን የዋጋ ማስተካከያን (Price Adjustment) መመርያን መሰረት በማድረግ ውሎች እንዲታደሱ ተደርገው የኮንስትራክሽን ስራዎች እንዲቀጥሉ ይደረግ ዘንድ ስምምነት ላይ ተደርሶበታል። በዚሁም መሰረት የውል ማሳደስ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ በ2017 የባጀት አመት መጀመርያ ወራት ላይ እንዲታደሱ ተደርገው የተመደበልን በጀት ባማከለ መልኩ የግንባታ ስራዎች የሚቀጥሉ ይሆናል። መስራት የማይችሉ ኮንትራክተሮች ካሉ ደግሞ እየተለዩ (የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ሰኔ ላይ ባደረገው ስብሰባ ላይ የወሰነው አይነት) ውላቸው እንዲቋረጥ የሚደረግ ይሆናል።

## ሰንጠረዥ 2. የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ዝርዝር እና የአፈፃፀም ደረጃ

| ተ.ቁ. | የፕሮጀክቱ ስም | የፕሮጀክቱ አድራሻ | የፕሮክቱ ዋጋ | የፕሮጀክቱ አማካሪ | የፕሮጀክቱ ተቋራጭ | አፈፃፀም (%) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ፊዚካል | ፋይናንሻል |
| 1 | ሁለት G+4 የተማሪዎች ዶርሚተሪ | ምውፃእ ወርቂ ግቢ | 227369091.61 | አትኮን ኮንስትራክሽን | ክራፍትስ ኮንስትራክሽን | 40 | 29.65 |
| 2 | ሁለት G+4 የመማርያ ህንፃ | ምውፃእ ወርቂ ግቢ | 178934700.62 | ኤምጂኤም አማካሪ | መገለታ ኮንስትራክሽን | 60.87 | 55.87 |
| 3 | የማስተማርያ ሆስፒታል ሎት 1 | ሆስፒታል ግቢ | 1599719212.21 | ኦቦን ቮያጅ አማካሪ | ተክለብርሃን አምባዬ | 3.18 | 3.18 |
| 4 | የማስተማርያ ሆስፒታል ሎት 2 | ሆስፒታል ግቢ | 1665516612.94 | ኦቦን ቮያጅ አማካሪ | አፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን | 3.5 | 3 |
| 5 | የተማሪዎች አገልግሎት ማእከል | ዋና ግቢ | 327892776.66 | ዮውሃን አባይ አማካሪ | ተክለብርሃን አምባዬ | 45 | 41.73 |
| 6 | G+8 የአስተዳደር ህንፃ | ዋና ግቢ | 554772593.57 | ዮውሃን አባይ አማካሪ | ዮቴክ ኮንስትራክሽን | 60 | 50 |
| 7 | የቆሻሻ ውሃ ማጣርያ ፕላንት | ዋና ግቢ | 161837506.09 | ኤምኤች አማካሪ | ዩናይትድ ኮንስትራክሽን | 72 | 68 |
| 8 | የግቢ ስነውበት (ላንድስኬፕ) | ዋና ግቢ | 87633639.66 | ዮውሃን አባይ አማካሪ | ተክለብርሃን አምባዬ | 55 | 49 |
| 9 | የውሃ መስመር ዝርጋታ | በተለያዩ ቦታዎች | 63224155.06 | ገሬታ አማካሪ | ደመራ ኮንስትራክሽን | 92 | 90 |
| 10 | የእንስሳት እርባታ ህንፃዎች | ምውፃእ ወርቂ ግቢ | 61137302.10 | ገሬታ አማካሪ | ሮሖምዓ ኮንስትራክሽን | 80 | 75 |
| 11 | የፍሳሽ ማጠራቀሚያና ማስወገጃ | በተለያዩ ቦታዎች | 27427441.15 | ገሬታ አማካሪ | ደመራ ኮንስትራክሽን | 90 | 85 |
| 12 | የአጥር ስራ | ምውፃእ ወርቂ ግቢ | 13811452.56 | ገሬታ አማካሪ | ቦንድ ኮንስትራክሽን | 66 | 65 |
| 13 | የተለያዩ ህንፃዎች ጥገና ሎት 1 | ዋና ግቢ | 36572958.28 | ኤዲኤስ አማካሪ | ሃይለማርያም ሕሉፍ | 58 | 54.67 |
| 14 | የተለያዩ ህንፃዎች ጥገና ሎት 2 | ዋና ግቢ | 33806314.57 | ኤዲኤስ አማካሪ | ተስፋሁን ጥዑማይ | 68 | 65 |
| | ድምር | | 5039655757.08 | | | | |

## 5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች

ዩኒቨርሲቲው ካሉት ሶስት ተልእኮዎች ውስጥ ሁለቱ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን የሚመለከቱ ናቸው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚከናወኑ የምርምር ስራዎች የፋይናንስ ምንጫቸው የሚገኘው ከዩኒቨርሲቲ መደበኛ በጀት ከሚመደብ ገንዘብ እና ከውጭ የተለያዩ ግንኙነቶችን በማድረግ ከሚገኝ ገንዘብ ነው። ከዩኒቨርሲቲው በጀት ለምርምር ስራዎች የሚመደበው በጀት በውድድር የሚመደብ ሲሆን የውድድር ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ በማድረግ ላሸነፉት ፕሮፖዛሎች በጀት ተመድቦላቸው የምርምር ስራዎች ይከናወናሉ። የምርምር ስራዎች በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን አነስተኛ (Small)፣ መካከለኛ (Medium) እና ትላልቅ (Large) የሚባሉት ናቸው። አነስተኛ የሚባሉት በአንድ አመት የሚጠናቀቁ ሲሆን መካከለኛ በሁለት አመት፣ ትላላቅ ደግሞ ከሁለት አመት በላይ የሚወስዱ የምርምር ስራዎች ናቸው። ዘንድሮ ከመደበኛ በጀት የተመደበው ለመካከለኛ ፕሮጀክቶች ነው። በዚሁም መሰረት ለውድድር የቀረቡ እና የተመረጡ የምርምር ፕሮፖዛሎች ብዛትና የተመደበው የምርምር በጀት መጠን በየኮሌጁ በሚከተለው ሰንጠርዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 3፤ ለውድድር የቀረቡ፣ ተቀባይነት ያገኙና ከዩኒቨርሲቲ መደበኛ በጀት የተመደበላቸው መሓከለኛ ደረጃ ያላቸው (MEDIUM) የምርምር ፕሮፖዛሎች

| ተ.ቁ. | ኮሌጅ/ትምህርት ቤት/ኢንስቲትዩት | ለግምገማ የቀረቡ የምርምር ፕሮፖዛሎች | ተቀባይነት አግኝተው በጀት የተመደበላቸው ፕሮፖዘሎች | የተመደበው በጀት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምህንድስናና ቴክኖሎጂ | 18 | 9 | 1444000.00 |
| 2 | ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 7 | 4 | 798880.25 |
| 3 | ህክምናና ጤና ሳይንስ | 15 | 5 | 999469.00 |
| 4 | ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 15 | 5 | 799504.01 |
| 5 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 6 | 4 | 799264.00 |
| 6 | ማህበረሰብና ስነሰብ | 8 | 4 | 798392.00 |
| 7 | ህግ ትምህርት ቤት | 2 | 2 | 399988.00 |
| 8 | በለስ ኢንስቲትዩት | 3 | 2 | 400000.00 |
| ድምር | | 74 | 35 | 6439497.26 |

በነዚህ የምርምር ፕሮፖዞሎች ውስጥ ከ130 መምህራን በላይ በመሳተፍ ላይ የሚገኙ ሲሆን ምርምርሮቹ የመካከለኛ ደረጃ ያላቸው ስለሚሆኑ በሚቀጥለው የትምህርት አመት (ማለትም 2017 የሚጠናቀቁ ይሆናል)። በዚህ መልኩ በየኮሎጁ በመከናወን ላይ ያሉት ምርምሮች ዝርዝር በእዝል 2 (በሪፖርቱ መጨረሻ ገፆች) ይገኛል።

ከላይ ሰንጠረዥ 3 የተመለከቱት የምርምር ፕሮፖዛሎች በዩኒቨርሲቲው በጀት በመሰራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በተለያየ መንገድ በሚገኝ ገንዘብ የሚሰሩ የምርምር ስራዎች ደግሞ ይኖራሉ። በዚህም መሰረት ከውጭ በሚገኝ በጀት በመሰራት ላይ የሚገኙት የምርምርና የማማከር ስራዎች ዝርዝራቸው በሚቀጥለው ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 4) የተመለከቱት ናቸው።

**ሰንጠረዥ 4፤ ከዩኒቨርሲቲው በጀት ውጭ በተገኘ ገንዘብ በመሰራት ላይ የሚገኙ የምርምርና የማማከር ስራዎች**

| S.No. | Project Title | Funding from | Budget (ETB) |
|---|---|---|---|
| 1 | ADU-ORE project on the training and upgrading of skills for lawyers | Operation Rescue Ethiopia | 360,000 |
| 2 | Stability and socio-economic development for vulnerable and marginalised communities in the Tigray region of Ethiopia | European Union Trust Fund* | 23430250.00 |
| 3 | Peace building, legal services, and MPSS<br>a) Human Security Trends, Challenges and Prospects in the Post-war Period: The case of Eastern Zone of Tigray Region<br>b) The role and practice of informal justice system in peace building post-war Tigray, the case of Eastern zone<br>c) Integrating post-traumatic growth, mental health and psychosocial support into peace building initiatives: A Holistic Psychological Approach into the post-war Tigray | CST Ethiopia** | 2500000.00 |
| 4 | Preparation of Basic Plan of Weini Town, Tigray | Tigray Beareau of Plan and Finance | 1,388,032 |
| 5 | Preparation of Basic Plan of TsediaTown, Tigray | Tigray Beareau of Plan and Finance | 1,944,278 |
| 6 | Urban Plan policy, post-war rehabilitation and software training to urban planning experts of Tigray Regional State | Tigray Beareau of Plan and Finance | 1,199,600 |
| 7 | AHORE Project | AHORE | 2,860,000 |
| 8 | Adigrat City Asphalt Road Project | Adigrat City Administration | 1200000.00 |
| | | **Total** | **34522160.00** |

* 187442 Euro

** 20000 Euro

በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ በጀት ውጭ በተገኘ በጀት በማከናወን ላይ የሚገኘው የምርምር እና የማማከር ስራዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በተደረጉ ስምምነቶች የሚከናወኑ ሲሆን አጠቃላይ የበጀት መጠኑ ደግሞ ከ34 ሚልዮን በላይ መሆኑ ለማወቅ ይቻላል።

በትምህርት አመቱ ሁለት አለምአቀፍ ኮንፈረንሶች የተካሄዱ ሲሆን እንዚህም (1) $6^{th}$ International Meskel Conference on “Post-War Heritage Reciver” የሚል መስከረም 2016 የተካሄደው እና (2) International Workshop on Materials for Sustainable Energy Applications: A Collaboration Between Adigrat University and University of Nottingha በሚል የካቲት 2016 የተካሄደው ነው

ዩኒቨርሲቲው በጦርነቱ ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት አንፃር እና በአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲውን ተልእኮዎች ከማሳካት አንፃር የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በስፋት ባሳተፈ መልኩ ፕሮፖዛሎችና ኮንሰፕት ኖቶች (Concept Notes and Proposals) በማዘጋጀት ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ስራዎች ማከናወን አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የዩኒቨርሲቲው ሲንየር ባለሞያዎች (መምህራን) ያካተቱ ሶስት ቲሞች ተቋቁመው ሰፋፊ እንቅስቃሴዎችን አከናውነዋል። ለሶስቱ ቲሞች የተሰጡዋቸው የስራ መስኮች (themes) የሚከተሉት ሲሆኑ፣

- Rehabilitating and Consolidating the University through Institutional Collaboration;
- Undertaking Research works mainly focusing on societal problem solving in view of the human, pshychological and material destruction caused by the war; and
- Overall enhancement of teaching, science, and technology

አንድ ቲም አንድ መስክ (theme) በመውሰድ የፕሮፖዛሎች ዝግጅት እንዲያከናውን እና ከፕሮፖዛል ዝግጅት ቀጥሎም ለስራው አፈፃፀም ይረዳ ዘንድ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ማሰባሰብ ስራዎች እንዲሰራ ስምምንት ላይ ተደርሶበት እንቅስቃሴዎች ተከናውነዋል። ለያንዳንዱ መስክ 12 ባለሞያዎች የተመደቡ ሲሆን በተለይ የመጀመርያውን መስክ የወሰደ የባለሞያዎች ቡድን ከሌሎች ቡድኖች እጅግ የተሻለ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ከፕሮፖዛል ዝግጅት አልፎ የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት፣ ኤምባሲዎችና የአገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመገኛነት ውጤታማ ሊባል የሚችል ስራ አከናውኗል። የተወሱ የቁሳቁስ ድጋፎችም ሊያገኝ ችላል። የተዘጋጁ ፕሮፖዛሎችን መሰረት በማድረግ ሃብት ለማሰባሰብ

እና አለም አቀፍ ኮንፈረንስ ለማድረግ ዝግጅት ተደርጎ ስራው እየቀጠለ ይገኛል። ከሁሉም በላይ ግን የዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ በስፋት በማሳተፍ ውጤታማ ስራ መስራት እንደሚችል ትምህርት የተወሰደበት ሲሆን የተዘጋጁ ፕሮፖዛሎች በቀጣይ በአለምአቀፍ ውድድሮችም ለመሳተፍ እንድ ጥሩ ግብአት ሆነው ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ስራው በኮሚቴ ከሚሰራበት ደረጃ ተነስቶ ቋሚና ራሱን የቻለ ፅ/ቤት እንዲደራጅም ከወዲሁ የሚሰራበት ይሆናል።

ከምርምር ስራዎች ጋር ተያይዞ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በዚህ ዓመት አራት የአእምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት ያገኘ መሆኑም እዚህ ላይ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡ አራት ደግሞ በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎቶችን አስመልክቶ ዩኒቨርሲቲው በበጀት አመቱ የሰራቸው ሰራዎች አሉ። ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው። የዩኒቨርሲቲው ባህላዊና ማሕበራዊ እሴቶች ከመጠበቅና ከማጎልበት አኳያ በተለይ በከተማው በድምቀት የሚከበረው የመስቀል በአል አከባበር ላይ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ያደረገ ሲሆን የድህረ-ጦርነት ቅርስ አጠባበቅና አጠቃቀም አስመልክቶ በርካታ ተሳታፊዎችና የወረቀት አቅራቢዎች የተገኙበት አለም አቀፍ ኮንፈረንስም ከመስቀል በአል ጋር ተያይዞ በስነ ቅርስ ቱሩዝምና አርኪዮሎጂ የትምህርት ክፍሎች አዘጋጅነት እንዲካሄድ ተደርጓል። ሌላው የህብረተሰብ አገልግሎት ስራ በህግ ትምህርት ክፍል ሰር በተዋቀረው የህግ ድጋፍ ማእከል ያደረገው ስራ ነው። ማእከሉ እንደአዲስ ተደራጅቶ የህግ ድጋፍ ለተቸገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በማድረግ ላይ ይገኛል። በተለይም ከላይ በተጠቀሰው ከአውሮፓ ህብረት በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ አመካኝነት ማህበረሰባዊ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከዚሁ ፕሮጀክት ጋር ተሳስሮ የሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍልም የስነ ልቦና ድጋፎችን በመስጠት ላይ ይገኛል። አረጋዊያንን የሚረዱ በከተማው ያሉ ድርጅቶችን ዩኒቨርሲቲው የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ የተሰራ ሌላው የማህበረሰብ አገልግሎት ድጋፍ ነው። በዩኒቨርሲቲው ያለው የበለስ ኢንስቲትዩት የኮችኔል ትል መሰራጨት ለመከላከል እና የበለስ ተክል ለበለጠ ጥቅም ለማዋል የሚሰራቸው የማህበረሰብ አገልግሎት ደግሞ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው። በዚህ መስክ ሌላ ሊጠቀስ የሚገባው ተግባር የወልዋሎ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብ ለማጠናገር የተደረገው ድጋፍ ነው። ክለቡ በከተማው አስተዳደርና በዩኒቨርሲቲው የጋራ ባለቤትነት የሚተዳደር ሲሆን በ2016 የክልሉ የአንበሳ ካፕ ውድድር ተሳታፊ ሆኖ በሁለተኛነት ደረጃ አጠናቋል። በ2017 ደግሞ ከጦርነቱ በፊት ወደ ነበረበት የፕሪሚየር

ሊግ ውድድር ገብቶ እንዲወዳደር ስለተፈቀደለት ዩኒቨርሲቲው የሚያደርገው ድጋፍ በበለጠ መቀጠል እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

በዚህ ዓመት ዩኒቨርሲቲው ከፌደራልና ከክልል ቢሮዎች ጋር በመተባበር የሰጣቸው ብዙ ስልጠናዎችና ሰሚናሮች ነበሩ፡፡ በ2016 ክረምት ላይ (ሐምሌ እና ነሐሴ 2016) ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለ1151 መምህራን ለተከታታይ 25 ቀናት ልዩ የአቅም ግንባት ስልጠና፤ ከኢትዮጵያ እስታቲስቲክስ አገልግሎት ጋር በመተባበር ደግሞ ለ688 የግብርና ናሙና የሚሰበስቡ ሰልጣኞች ለተከታታይ 29 ቀናት ስልጠና።

ከስልጠና ጋር ተያይዞ ሌሎች የተሰሩ ስራዎችም በርካታ ናቸው። ከሰራዊት ለተመለሱ በስራ ክህሎት ዙርያ በግብርናና አከባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የተሰጠ ስልጠና፤ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅም ለ359 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የተሰጠ ስልጠና፤ ከክልል ስፖርት ፌደሬሽንና የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር የአንደኛ ደረጃ የአሰልጣኞች ስልጠና፤ ከጃፓይጎ ጋር በመተባበር በComputer based testing ዙርያ የተሰጠ ስልጠና፤ በምርምር ወረቀት አፃፃፍ ዙሪያ ከስፔስ ሳይንስ በመጡ እንግዳ ስልጠና ይገኙበታል፡፡ በኮሌራ በሽታ መከላከል ዙሪያ ላይም ከክልል ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ባለሞያዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው፤ ከዓይደር ሆስፒታል የተገኙ የህክምና ቁሳቁስ በዓዲግራት ሆስፒታል ICU ይረዳ ዘንድ በስጦታ መገኘቱ፤ በህክምናና ጤናሳይንስ ኮሌጅ ከዳኖን የምግብ ፋብሪካ (ፈረንሳይ አገር የሚገኝ ፋብሪካ ሆኖ ሃንጋሪ ላይ በመማር በሚገኙ የዩኒቨርሲቲያችን መምህራን አፈላላጊነትና አስተባባሪነት የተገኘ) የተገኘ 10 ሚልዮን ብር የሚያወጣ 1200 ካርቶን የህፃናት ወተት በድርቅ ለተጠቁ በአበርገለ፣ ኢሮብና ዓዲግራት ከተማ ለሚገኙ ህፃናት መከፋፈሉና ሌሎች በስልጠናና በማማከር አወንታዊ አበርክቶ አድርገዋል፡፡ በዚህ ዓመት በጦርነቱ ምክንያት የስነ ልቦና ጫና ለደረሰበት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በቂ ነው ባይባልም በስንልቦናዊ መነቃቃት ላይ አወንታዊ አስተዋፅኦ የሚኖራቸው የተለያዩ ኮንፈረንሶችና ዎርክሾፖች ተደርገዋል፡፡

## 6. በርካታ የተማሪዎች ፈተናዎች የተሰጡበት የትምህርት አመት

የ2016 የትምህርት ዘመን በርካታ ፈተናዎችን ያከናወንበት ዘመን ነው ሆኖ ያለፈው። መስከረም 2016 መጨረሻ ላይ የ12 ክፍል መልከቀቅያ ፈተና አካሂደናል። ይሄንን ፈተና ለማካሄድ ደግሞ ግቢው ውስጥ የነበሩ ተማሪዎችን ለሶስት ሳምንታት ከግቢው እንድናወጣ የተገደድንበት ሁኔታ ነው የነበረው፤ ምክንያቱም ተማሪዎች ግቢ ውስጥ እያሉ የአስራ

ሁለተኛ ተማሪዎች ፈተና ማካሄድ እንደማይቻል የትምህርት ሚኒስቴር መመርያ ስለሚያስገድድ ነው። ከዚሁ ቀጥሎም የድህረምረቃ መግቢያ ፈተና ህዳር 2016 ላይ በመስመር ላይ (Online) ተሰጥቷል። ጥር 2016 ላይ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች መውጫ ፈተና በመስመር ላይ ተከናውኗል። በዚሁ ፈተና የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እና ከግል ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተፈታኞች በዩኒቨርሲቲው ተስተናግደዋል። በዩኒቨርሲቲው ከተፈተኑት 109 ተፈታኞች ውስጥ አምስት ተፈታኞች ብቻ የወደቁ ሲሆን በመቶኛ ሲገለፅ 95.42% ያህል ማለፍ ችለዋል።

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ተመድበው ሲማሩ የቆዩት የሬሜዲያል ተማሪዎችም የኦንላይን ፈተና ግንቦት ላይ እንዲወስዱ ተደርገዋል። ሰኔ 2016 ላይ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና የወሰዱበት ነበር። የተፈታኝ ተማሪዎች ብዛት እንዲሁም በፈተናው ያለፉና ያላለፉ በሚከተለው ሰንጠርዥ ላይ ተጠቃሎ ቀርቧል፤

ሰንጠረዥ 5፤ ሰኔ 2016 ላይ የመውጫ ፈተና የወሰዱ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች

| ኮሌጅ | የተፈታኞች በዛት | የማለፍያ ነጥብ ያመጡ (>= 50 %) | የማለፍያ ነጥብ ያላመጡ (<= 50%) | የማለፍያ ነጥብ ያመጡት % |
|---|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 583 | 498 | 85 | 85.42 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 38 | 26 | 12 | 68.42 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 60 | 40 | 20 | 66.67 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 76 | 55 | 21 | 72.37 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 208 | 91 | 117 | 43.75 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 11 | 9 | 2 | 81.82 |
| ህግ ትምህርት ቤት | 25 | 17 | 8 | 68.00 |
| ድምር | 1001 | 736 | 265 | 73.53 |

በድምሩ በአመቱ የመውጫ ፈተና (Exit Exam) የወሰዱ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ብዛት 1110 ሲሆን ከዚህም ማለፍያ ነጥብ ያመጡት 840 (ወይም 75.68%) ሲሆን የማለፍያ ነጥብ ያላመጡት ደግሞ 270 (ወይም 24.32%) ናቸው። በመቶኛ ሲሰላ የማለፍያ ነጥብ ካላመጡት ተማሪዎች ውስጥ  የሚበዙት የተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች መሆናቸው ለማወቅ ተችሏል።

ሐምሌ 2016 መጀመርያ ላይ ደግሞ የ12 ክፍል መውጫ ፈተና ተፈታኞች ለፈተና የተቀመጡበት ጊዜ ነው የነበረው። የተሰጠው ፈተና በሁለት አይነት (Hibrid) ማለትም በወረቀት እና በኦንላይን ነው የነበረው። በ12 ክፍል ማጠቃለያ ፈተና የተፈተኑት ተማሪዎች ብዛት 8108 የነበረ ሲሆን በከፍተኛ ጥንቃቄና ክትትል የተደረገ ነው የነበረው። የፈተናውን ሂደት የሚያካሂዱ በርካታ ፈታኞች እና አስተባባሪዎች ከመላው የአገሪቱ ክፍል ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ የፈተናውን ደህንነትና ፀጥታ ለማረጋገጥ ከፌደራል ፓሊስ ብዛት ያላቸው ፓሊሶች ተመድበው ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል። የአከባቢው ፖሊስም የፀጥታና ደህንነት ስራውን በማገዝ ረገድ የነበረው ሚና ትልቅ ነበር። ዩኒቨርሲቲው በዋናነት የመኝታና የምግብ አቅርቦት እንዲሁም የትራንስፖርትና የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመስጠት የተጠመደበት ሁኔታ ነው የነበረው። አጠቃላይ የፈተናው አስተዳደርም አስመልክቶ በዩኒቨርሲቲው ፕሪዚደንት የሚመራ ኮማንድ ፖስት ተቋቁሞ በየቀኑና በየሰአቱ የማስተባበርና የክትትል ስራዎችን በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል።

በአጠቃላይ በትምህርት አመቱ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎቹ ከሚያደርጋቸው መደበኛ ፈተኛዎች በተጨማሪ ከላይ የተገለፁት በርካታ ፈተናዎች የተካሄዱበት አመት ነው የነበረው። እንዚህን ተጨማሪ ፈተናዎች ማስተዳደር በዩኒቨርሲቲው ተጨማሪ የስራ ጫና የፈጠረ ሲሆን በተለይ በኦንላይን የሚሰጡ ፈተናዎች የሃይል መቆራረጥን ለማስወገድ በጀነሬተር እየታገዙ ይካሄዱ ስለነበር ከፍተኛ የወጪ ጫናም መፍጠራቸው አልቀረም። ለማንኛውም ግን ዩኒቨርሲቲው ፈተኛዎቹን በተሳካ ሁኔታ ያከናወነበት እና የፈፀመበት አመት ሆኖ ነው ያለፈው።

## 7. ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እና ዓዲግራት አጠቃላይ ሆስፒታል

የዩኒቨርሲቲው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስራውን የጀመረው 2005 ላይ ነው። ኮሌጁ ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በዓዲግራት ከተማ ከሚገኘው አጠቃላይ ሆስፒታል በመደጋገፍና በጋራ ሲሰሩ ቆይተዋል። ዩኒቨርሲቲው ለሆስፒታሉ በርካታ ድጋፎችን ያደረገ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች የተግባር ልምምዳቸውን የሚያደርጉት ደግሚ በዚሁ ሆስፒታል ላይ ነው። ስለዚህ ተደጋግፎ መስራቱ የጋራ ተጠቃሚነትን በማዳበር መስክ የላቀ ድርሻ ነበረው። ከድጋፎቹ ሊጠቀስ የሚችለው በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ዩኒቨርሲቲው ያስገነባው ባለአንድ ፎቅ ህንፃ ሲሆን ሌላው ተጠቃሽ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው የህክምናና ጤና ባለሞያዎች በሆስፒታሉ ሰፊ አገልግሎት

የሚሰጡ መሆናቸው ነው። እንደተጠቀሰው ደግሞ የኮሌጁ ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድና ትምህርት የሚወስዱት በዋናነት በሆስፒታሉ መሆኑ ተደጋጋፊነቱ ያለው ጠቀሜታ የሚያመላክት ነው።

ከዚሁ ጎን ለጎን ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ የመማርያ (ወይም ኮምፕረሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) ግንባታ ለማድረግ በቂ ቦታ ተረክቦ የካሳ ክፍያ አጠናቆ፣ በጨረታ አሸናፊዎች ተለይተው በሁለት ኮንትራክተሮች የሚሰራ የሆስፒታል ግንባታ 2012 የትምህርት ዘመን መጀመርያ ላይ የጀመረ ሲሆን ግንባታው በጦርነቱ ምክንያትቆሞ ይገኛል። የገንባታ ስራው ግን አስፈላጊ አስተዳደራዊ ስራዎች ተደርገው የሚቀጥል ይሆናል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰርቶ ይጠናቀቃል የሚባል ግን አይደለም።

የመማርያ ሆስፒታሉ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ከመጠበቅ ይልቅ የከተማው ሆስፒታል ከዩኒቨርሲቲው ተዋህዶ እንዲሰራ ቢደረግ የተሻለ ጥቅም እንደሚገኝበት ስለታመነበት የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቦርድ ታህሳስ 06/2016 ባደረገው ስብሰባ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ለትግራይ ክልል ጤና ቢሮ ዩኒቨርሲቲው እና ሆስፒታሉ እንዲዋሃዱ ፍላጎት ያለው መሆኑን በደብዳቤ ጥያቄ አቅርቧል። በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች በተመሳሳይ መልክ በከተማቸው የሚገኙ ሆስፒታሎች ከዩኒቨርሲቲዎቹ ጋር እንዲዋሃዱ ተደርገው እየሰሩ እንደሚገኙ ይታወቃል። የዓዲግራት ሆስፒታል ከዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ጋር ተዋህዶ እንዲሰራ ማድረግ ሁለት ዋና ዋና ጥቅሞች እንዳሉት ይታመንበታል። በአንድ በኩል በሆስፒታሉ ሁለት የተለያዩ አካላት (ማለትም የዩኒቨርሲቲው ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ሆስፒታሉ ራሱ) በየራሳቸው መንገድ እንዲሰሩ ከሚደረግ ራሱን የቻለ እና ወጥነት ያለው አስተዳደር እንዲኖረው ያስችላል። የአስተዳደር እና የስራ መዋቅሩ ወጥነት ያለውና የታወቀ የእዝ መስመር ያለው እንዲሆን ያደርገዋል። ወጥነት በሌለው እና የእዝ መስመሩ በተምታታ አካሄድ ምክንያት የሚፈጠረው ችግርም ለመቅረግ ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ሆስፒታሉ አሁን ያለበት ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታለ የሚል ሲሆን ደረጃውን ወደ ኮምፕረሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በማሳደግ ከደረጃው ማደግ ጋር የሚገኙ ጥቅሞችን ለማግኘት ያስችለዋል። ቀድሞ በክልል ደረጃ ይመደብለት ከነበረው በጀትም የተሻለ በጀት በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የሚመደብለት ይሆናል። በባለሞያዎች በኩልም ዩኒቨርሲቲው በቂ የህክምና ባለሞያዎች ያሉት ሲሆን የነዚህ ባለሞያዎች ችሎታም በአግባቡ ለመጠቀም ያስችለዋል። በነዚህ ሁለት ምክንያቶችም ሆስፒታሉ ልህብረተሰቡ የተሻለና ያደገ አገልግሎት መስጠት

ይችላል። የህክምናና ጤና ባለሞያዎችም የበለጠ እውቀት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ኮሌጁ የስፔሻላይዝድ ትምህርቶችም ለመጀመር ያስችለዋል። ዩኒቨርሲቲው ቅድሚያ ሰጥቶ ለመስራት በራእዩና ተልእኮው ካስቀመጣቸው ነገሮች ውስጥ በህክምናና ጤና ሳይንስ ስራዎች የልህቀት ማእከል (Center of Excellence) እንዲሆን ማስቻል ነው።

በዚሁም መሰረት የመዋሃድ ጥያቄው ለክልሉ ጤና ቢሮ የተጠየቀ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎንም ዩኒቨርሲቲው የኮምፕረሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የስራ መዋቅር ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አቅርቦ በትምህርት ሚኒስቴር ተደግፎ ያስፀደቀ ሲሆን ለገንዘብ ሚኒስቴር ለ2017 የበጀት አመት ለሆስፒታሉ በጀት እንዲመደብለት ጠይቆ በጀት ተፈቅዶለታል። የመዋሃዱ ጥያቄም በሚመለከታቸው የክልል እና የከተማው አካላት ውይይት እየተደረገበት ሲሆን በቅርቡ እልባት ያገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ሁለቱም እንዲዋሃዱ ከተደፈቀደ የሚከተሉት ዋና ዋና ስራዎች ለ2017 የትምህርት ዘመን እንዲሰሩ የታሰቡት የሚከተሉት ናቸው፤

- ከውሃና ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ጋር የተያያዙ ጥገናዎችን ማከናወን
- የግድግዳ ቀለሞች መቀባትና ሌሎች የጥገና ስራዎችን ማከናወን
- አዲስ በፀደቀው የስራ መዋቅር መሰረት ወጥ የሆነ የሰራተኛ ምደባ እና የሃላፊዎች ምደባ ማከናወን
- የፅዳት ስራውን ወደ ውጭ በማውጣት እንዲሰራ በማድረግ የተሻለ አገልግሎት እንዲገኝ ማድረግ
- ሆስፒታሉን ከዩኒቨርሲቲው ዳታ ሰንተር እንዲያያዝ በማድረግ የኔትወርክ እና የኢንተርኔት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ እና የሆስፒታሉን አገልግሎት ለማዘመን የሆስፒታል አገልግሎት ሶፍትዌር እንዲዘጋጅ በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ
- የተሻለ የኬሚካሎችና የመድሃኒቶች አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ
- አዲስ የላውንድሪ ህንፃ እንዲገነባ በማድረግ የተሻለ አገልግሎት መስጠት
- አስፈላጊ ነው ተብለው የታመነባቸውና የህክምና አሰጣጥ ደረጃውን ሊያሳድጉ የሚችሉ መሳርያዎች እንዲገዙ ማድረግ
- በሆስፒታሉ ላይ ያሉ ነገር ግን ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሳርያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ

## 8. በዩኒቨርሲቲው ስለሚገኙ የላቦራቶሪዎችና እና ዎርክሾፕ ሁኔታ (Laboratories and Workshops)

በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው የዩኒቨርሲቲው መሰረተልማቶች ውስጥ ላቦራቶሪዎችና ይገኙበታል። እነዚን በተመለከተ በበጀት አመቱ ብዙ የተሰራ ስራ አለ ባይባልም በ2017 የትምህርት ዘመን ከፍትኛ ትኩረት ተሰጥቶዋቸው መሰራት ካለባቸው ጉዳዮች ውስጥ የሚመደቡ ይሆናል። በዚሁም መሰረት ዝግጅቱ ከ2016 በጀት አመት መጀመር ስለሚኖርበት የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ከሚመለከታቸው ኮሌጆች (ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ፣ ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ፣ እንዲሁም ግብርናና አከባቢ ሳይንስ ኮሌጅ) ጋር በመሆን ሰኔ ወር ላይ የአንድ ሳምንት የመስክ ጉብኝትና ውይይት ተከናውኗል።

በጉብኝቱ ወቅት ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች ያሉበት ሁኔታ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በርካታ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል። በጉብኝቱ ወቅት የተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፤

- በየቦታው በርካታ የተዘረፉና የተበላሹ እቃዎች/ሚሽኖች/ማቴርያሎች መኖራቸው የታወቀ ሲሆን ከተበላሹት ውስጥ ከፊሎቹ ከአገልግሎት ውጭ የተደረጉ ከፊሎቹ ደግሞ አገልግሎት እንዲሰጡ የጥገና ስራ የሚፈልጉ ማቴርያሎች/ሚሽኖች መኖራቸው፤
- በአሁኑ ጊዜ ካዳቫር ማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ በቨርቹዋል ካዳቫር ለመስራት እንዲቻል የቴሌቪዥን አቅርቦት እንደሚያስፈልግ፤
- የውሃ አቅርቦት አለመኖር፣ ኤሌክትሪክ የማይሰራባቸው አከባቢዎች መኖር፣ የተዘረፉ ብሬከሮች እና የተበጣጠሱ ገመዶች መኖራቸው፤
- ጥቅም ላይ ያልዋሉ እና ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች በብዛት በየቦታ መኖራቸው፣ በአንድ ቦታ ላይ ትርፍ ኬሚካሎች እያሉ በሌላ ቦታ ላይ ተገዝተው የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ፣ ጊዜ ያለፈባቸው ቢሆኑም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት ተለይተው ያልተቀመጡ መሆናቸው፤
- በቀጥታ በመድፍ የተመቱ ህንፃዎች (ለምሳሌ የኬሚካል ምህንድስና ላቦራቶሪ) እና መስተዋታቸው በፍንዳታ ምክንያት የተሰባበሩ ህንፃዎች/ክፍሎች በብዛት መኖራቸው፤
- ቀደም ብለው ሲሰሩ ጉድለት የነበረባቸው (ለምሳሌ የባስኬት ቦል መጫወቻ ሜዳ) ነገሮች መስተዋላቸው፤

- በዎርክሾፖችና በላቦራቶሪዎች ስለሚገኙ እቃዎችና ግብአቶች ኢንቨንተሪ በአግባቡ ያልተካሄደባቸው እና ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፤
- የተበላሹትና የወዳደቁት ኬሚካሎች እና ሌሎች ነገሮች ለማስወገድና ለማፅዳት ተፈላጊ የሆኑ የPPE (Personal Protective Equipment) አቅርቦት አለመኖር፤
- በላቦራቶሪዎች እና ዎርክሾፖች የተመደቡ የቴክኒካል ረዳት ባለሞያዎች በስራ ሰአት በቦታቸው የማይገኙ መሆን፤
- በርካታ ትምህርት ክፍሎች እና ኮሌጆች ሊጠቀሙበት የሚችል የጋራ የሆነ ላቦራቶሪ ያልተደራጀ መሆኑ። ለምሳሌ የBioTechnology ትምህርት ክፍልና College of Agriculture በጋራ ሊጠቀሙ የሚችሉበት የGreen House ያልተሰራ መሆኑ፤
- ሃይለኛ የፀሃይ ብርሃን የሚገባባቸው እና ወለላቸው ለስራ አመቺ ያልሆኑ ክፍሎች (ለምሳሌ የነርሲንግ እና ሚድ ዋይፈሪ ላቦራቶሪ) መኖራቸው።

የተደረገውን ጉብኝት ተከትሎ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ላቦራቶሪዎች፣ ዎርክሾፖች እና የስፖርት ሜዳዎች (ጂሞችንም ጨምሮ) አስመልክቶ ለ2017 የትምህርት አመት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶዋቸው መሰራት እንዳለባቸው ስምምነት ላይ በመድረስ ያልጀመሩትን ለማስጀመር እንዲሁም ስራ ላይ ያሉትን የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ አቅጣጫዎች መከተል እንደሚገባ አቅጣጫ ሰጥቶበታል።

የመፍትሄ አቅጣጫዎች

- ለዩኒቨርሲቲው የተመደበው በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት በ2017 የትምህርት ዘመን መጀመርያ ላይ ስራ ለመጀመር አስፈላጊ ናቸው የተባሉትን ማቴርያሎችና ግብአቶች ትኩረት በማድረግና በመለየት የግዥ ጥያቄዎችን ማቅረብ፤
- ማቴርያሎችን በመዋዋስ ወይም ሼር በማድረግ ጥቅም ላይ ማዋል (ይህ በአንድ ኮሌጅ ስር የሚገኙ ትምህርት ክፈሎች ብቻ ሳይሆን ከኮሌጅ ኮሌጅ በመዋዋስ ወይም ሼር በማድረግ የሚሰሩትን ስራዎች ይመለከታል። (በጉብኝቱ ወቅት በአንድ ቦታ ተፈላጊ የሆነ እና የሌለ እቃ በሌላ ቦታ ያለጥቅም የተቀመጠበት ሁኔታ እንዳለ ተስተውሏል። (ለዚህ እንደ ጥሩ ምሳሌ Oven መጥቀስ ይቻላል)፤
- ከአንድ በላይ ትምህርት ክፍሎችና ኮሌጆች ሊጠቀሙበት የሚችል ላቦራቶሪ በሂደት እንዲደራጅ ማድረግ፣ እና

- መሰራት ያለባቸውን ስራዎች በየክፍሉና በየእርከኑ (በትምህርት ክፍል፣ በኮሌጅ፣ በመሰረታዊ አገልግሎት፣ በዩኒቨርሲቲ አስተዳደር) ተከፋፍለው እንዲሰሩ በማድረግ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ።

ከላይ በተቀመጡት አቅጣጫዎች በተለይም ስራዎችን በየደረጃውና በየእርከኑ ተከፋፍሎ መሰራት ይገባዋል ተብሎ በተቀመጠው መሰረት ሃላፊነቶች በሚመለከተው መልኩ እንዲከናወኑ አስተዳደር ካውንስሉ ስምምነት የደረሰበት ሲሆን የሚመለከተው ክፍል ሃላፊነቱን ወስዶ ተገቢው ስራ ማከናወን ይኖርበታል፤

በኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች መሰራት ያለባቸው ተግባራት

1. የእቃዎችና ግብአቶች ዝርዝር ኢንቨንተሪ በማከናወን በአግባቡ ተመዝግቦ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ማድረግ፤
2. ያለውን የበጀት እጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት እና ስራ ለማስጀመር አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችንና ማቴርያሎችን ብቻ በመለየት የግዥ ጥያቄዎችን ማቅረብ። በ2017 የበጀት አመት ግዥ የሚከናወነው በ EGP (Electronic Government Purchase) ስርአት በመሆኑ እና ይሄንን አስመልክቶ ደግሞ በየደረጃው ላሉት ሃላፊዎች ስልጠና የተሰጠ በመሆኑ የግዥ ጥያቄዎች በተሰጠው ስልጠና መሰረት በጊዜው እንዲቀርብ ማድረግ፤
3. በየቦታው ያሉት ኬሚካሎች አስመልክቶ በተራ ቁጥር 1 በተቀመጠው መሰረት ኢንቨንተሪ ተደርጎ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉና ፈፅሞ ሊሰጡ የማይችሉ (ወይም መወገድ ያለባቸው) ተለይተው እንዲመዘገቡ ተደርጎ ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲ አስተዳደር እንዲደርስ ማድረግ፤
4. ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች በስራ ሰአትና በትምህርት ሰአት ለስራ ክፍት መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፤
5. PPEን ጨምሮ ሌሎች ተፈላጊ ግብአቶች አስመልክቶ የግዥ ጥያቄ ማቅረብ፤
6. ጥገና ተደርጎላቸው ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ ተብለው የሚታመንባቸው እቃዎች/ማቴርያሎች/ሜሽኖች በተገቢው በመለየት እና ጥገናውን የሚያከናውኑ ባለሞያዎችን በማፈላለግ ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ማቅረብ፤
7. በመዋዋስና ሼር በማድረግ ጥቅም ላይ የሚውሉትን በመለየትና በመመዝገብ ለጋራ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ (ይህ በትምህርት ክፍሎች እና በኮሌጆች መሃከል የሚደረግ ይሆናል)፤ እና

8. የኤሌክትሪክ (ብሬከሮች፣ ገመዶች፣ ወዘተ)፣ የውሃ መስመር፣ የመስተዋት እና የህንፃ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ለይቶ ለመሰረታዊ አገልግሎት እንዲቀርቡ ማድረግ።

በመሰረታዊ አገልግሎት እና በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር መከናወን ያለባቸው ተግባራት

1. የኤሌክትሪክ ጥገና ማከናወን። ከሚመለከታቸው ኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች ጋር በመሆን ጥገና የሚያስፈልገው የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ ገመዶች፣ ብሬከሮች ወዘተ በመለየት እንዲጠገኑ ማድረግ።
2. የውሃ መስመር ጥገናዎች ማከናወን፤ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የውሃ መስመሮች ከሚመለከታቸው ኮሌጆችና ትምህርት ክፈሎች ጋር በመሆን በመለየት የጥገና ስራዎችን ማከናወን። እንደ ጥሩ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚገባው በተፈጥሮ ሳይንስ ላቦራቶሪዎች ተሰርቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሮ የነበረው የውሃ ታወር ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣ እንዲሁም በበርካታ ኮሌጆች የሚገኙ ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች የውሃ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ የተሰራው ሁለተኛው የውሃ ታወር አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ።
3. የተሰባበሩ መስተዋቶች ጥገና ማከናወን።
4. በመድፍ/ሞርታር ከተመቱት ህንፃዎች ውስጥ በቶሎ መጠገን ያለባቸውን በመለየት እንዲጠገኑ ማድረግ።
5. በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ ለአገልግሎት አይበቁም ተብለው የተለዩ ኬሚካሎች በዘላቂነት እስኪወገዱ ድረስ በጊዜያዊነት ሊቀመጡ የሚችሉበት ቦታ በመለየት እንዲቀመጡ ማድረግ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለዚህ የሚሆን የተለየ ህንፃ እንዲሰራ በማድረግ መወገድ ያለባቸው በጊዜያዊነት እንዲቀመጡ ማድረግ።
6. የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተጠየቁት ቴሌቪዥኖች እንዲቀርቡ ማድረግ። ከፍተኛ የፀሃይ ብርሃን የሚገባባቸው እና ወለላቸው ለስራ አመቺ ያልሆኑትን በመለየት የመጋረጃ እና የወለል ስራ ማከናወን።
7. በየትምህርት ክፍሉ እንዲጠገኑ የተለዩትን እቃዎች/ማቴርያሎች/ማሽኖች መሰረት በማድረግ የጥገናውን ስራ ሊያከናውኑ የሚችሉና በየኮሌጁ/ትምህርት ክፍሉ ጥገናውን ሊያከናውኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩትን አካላት መሰረት በማድረግ የጥገና ስራዎች እንዲከናወኑ ማድረግ። እና

8. በርካታ ትምህርት ክፍሎችና ኮሌጆች ሊጠቀሙበት የሚችሉ የጋራ ላቦራቶሪ ሊደራጅ የሚችልበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው ኮሌጆች ጋር በመነጋገር በሂደት እንዲደራጅ የማስተባበር ስራ መስራት።

## 9. የበጀት አጠቃቀም

ዘንድሮ ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደው ባጀት ሊሰራ ከተፈለገው ጋር የሚመጣጠን አይደለም። የገንዘቡ የመግዛት አቅምም በጣም እንደተዳከመ የሚታወቅ ነው። ከታች በሰንጠረዥ 6 እንደተመለከተው ለ2016 የበጀት አመት መጀመርያ የተፈቀደው በጀት ብር 828,067,720.00 በስራ ሂደት ተስተካክሎ የተፈቀደልን በጀት ደግሞ ብር 1,325,167,720.00 ነው። ከዚሁ ውስጥ ለመደበኛ በጀት የተፈቀደልን ብር 575,167,720.00 ሲሆን ለካፒታል በጀት የተፈቀደልን ደግሞ 750,000,000.00 ነው። በአመቱ መጨረሻ የነበረን የበጀት አጠቃቀም በአጠቃላይ 98.56% ሲሆን የመደበኛ በጀት 99.55% የካፒታል በጀት ደግሞ 97.81% ነው። የካፒታል በጀት አጠቃቀሙ በአድቫንስ መልክ የተሰጠውንም የሚያካትት ሆኖ የአመቱ የበጀት አጠቃቀማችን አጥጋቢ እንደነበረ ማየት ይቻላል። ሆኖም ግን በተለይ ለተማሪዎች የተመደበው በጀት በጣም አነስተኛ በመሆኑ (ለአንድ ተማሪ በቀን የተመደበው በጀት ብር 22.00 ነው) የምግብ በጀት ብቻ ተወስዶ ሲታይ የነገቲቭ ሚዛን የሚያሳይ ነው። ይህም ማለት የምግብ በጀትን ከሌላ የበጀት ርእስ እንዲሸፈን ተደርጓል ባለት ነው።

በጀቱን ወደ ኮሌጆችና ሌሎች የበጀት ማእከላት እንዲወርድ ስለማድረግ አስመልክቶ ልክ እንደተመደበልን መደበኛ በጀቱ አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲከፋፈል ተደርጓል። አጠቃቀሙን በተመለከተ ደግሞ ሶስት ኮሌጆች ማለትም ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ግብርናና አከባቢ ሳይንስ ኮሌጅ፣ እንዲሁም ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የራሳቸው የሰው ሃይል በመጠቀም ግዥዎችና ክፍያዎችን ማድረግ ችለዋል። ደመወዝም በተመሳሳይ መልኩ መክፈል ችለዋል። ሌሎቹ ግን በዋናው የግዥና የፋይናንስ አስተዳደሮች እየታገዙ በጀታቸውን መጠቀም ችለዋል።

ሰንጠረዥ 6. የ2016 የበጀት አጠቃቀም

| ተ.ቁ. | የበጀት አይነት | ፕሮግራም | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | ጥቅም ላይ የዋለ | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መደበኛ በጀት | 392-01-01 (አስተዳደር) | 127290720 | 161256720 | 160289172.8 | 99.40 |
| | | 392-02-01 (መማር ማስተማር ማከናወን) | 207235000 | 308928000 | 308562591.7 | 99.88 |
| | | 392-02-02 (ተማሪዎች አገልግሎት መስጠት) | 71080000 | 91515000 | 90620955 | 99.02 |
| | | 392-03-01 (ጥናትና ምርምር ማካሄድ) | 14658000 | 12268000 | 12013032.33 | 97.92 |
| | | 392-03-02 (ቴክኖሎጂ ሽግግር) | 4687000 | | | |
| | | 392-04-01 (ማህበረሰብ አገልግሎት | 3117000 | 1200000 | 1093160.3 | 91.10 |
| | መደበኛ በጀት ድምር | | 428067720 | 575167720 | 572578912.1 | 99.55 |
| 2 | ካፒታል በጀት | 392-01-01-01-001 (ውጭ መምህራን ደመወዝ) | 20470000 | | | |
| | | 392-01-01-01-002 (ተማሪዎች መኝታ ግንባታ) | 86705600 | 107175600 | 105175600 | 98.13 |
| | | 392-01-01-01-004 (ዎርክሾፕ ግንባታ) | 44087400 | 44087400 | 41087400 | 93.20 |
| | | 392-01-01-01-005 (አስተዳደር ህንፃ ግንባታ) | 40725000 | 39625000 | 38250000 | 96.53 |
| | | 392-01-01-01-006 (መሰረተ ልማት ግንባታ) | 86700000 | 438910000 | 438436606.3 | 99.89 |
| | | 392-01-01-01-007 (መኝታ ግንባታ) | 21650000 | 20540000 | 20540000 | 100.00 |
| | | 392-01-01-01-011 (ላቦራቶሪ ግንባታ) | 20362000 | 20362000 | 17362000 | 85.27 |
| | | 392-01-01-01-012 (ላይብረሪ ግንባታ) | 34650000 | 35760000 | 31445197.76 | 87.93 |
| | | 392-01-01-01-013 (ህንፃ ግንባታ) | 44650000 | 43540000 | 41246519.18 | 94.73 |
| | ካፒታል በጀት ድምር | | 400000000 | 750000000 | 733543323.2 | 97.81 |
| ጠቅላላ ድምር | | | 828067720 | 1325167720 | 1306122235 | 98.56 |

## 10. አዲስ የስራ መዋቅር አፈፃፀም

በበጀት አመቱ ከተከናወኑት አበይት ጉዳዮች ውስጥ የአዲስ የስራ መዋቅር (New Organizational Structure) አፈፃፀም ይገኝበታል። አዲስ ስትሪክቸር የማስፈፀም ጉዳይ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ቀደም ብሎ የተጀመረ ሲሆን ዩኒቨርሲቲያችን ግን ከግንኙነቱ ርቆ ስለነበር (በነበረው ጦርነት ምክንያት) ስራውን ዘግይቶ የጀመረው ቢሆንም ለአፈፃፀሙ ትልቅ ትኩረት በመስጠት በመጀመርያ መዋቅሩን በማዘጋጀት ለሲቪል ሰርቪስ የሚያቀርብ ኮሚቴ ተቋቁሞ ስልጠና እንዲያገኝ ተደርጓል። ቀጥሎ መዋቅሩ እንዲሰራና ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ እንዲፀድቅ ተደርጓል። መዋቅሩ ፀድቆ ከተላከልን በኋላ መዋቅሩን መሬት ላይ ለማውረድ የሚያስችሉ ስራዎች ለመስራት የሚያስፈልጉ ተግባራት እንዲከናወኑ ተደርጓል። በዚሁም መሰረት የደልዳይ ኮሚቴ አባላት እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በመመርያው መሰረት ከፊሎቹ በመላው ሰራተኛ እንዲመረጡ፣ ከፊሎቹ ደግሞ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እንዲመደቡ ተደርጎ ወደ ድልድል ስራ ነው የተገባው።
የድልድል ኮሚቴው በተቋቋመ ማግስት የድልድል ስራውን መከወን የጀመረ ሲሆን ለማጠናቀቅ የተወሰኑ ወራት ወስዶበታል። የድልድሉ ስራ በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ ተጠናቆ ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደርም የራሱን ግብአት ጨምሮበትና አፅድቆት መላው ሰራተኛ እንዲያውቀው የተለጠፈለት ሲሆን ለያንዳንዱ ሰራተኛ ደግሞ የድልድል ደብዳቤ እንዲደርሰው ተደርጓል።

ከታች በሰንጠረዥ 7 እንደተመለከተው ለድልድል ካመለከተቱት 1317 የአስተዳደር ሰራተኞች ውስጥ 1307 በመዋቅሩ መሰረት ተመድበዋል (አስር ሰራተኞች በሂደት ምደባውን አቋርጠዋል ወይም ዩኒቨርሲቲውን ለቀዋል)። ከተመደቡት ውስጥ 537 (40.8%) በአንደኛ ምርጫቸው፣ 374 (28.4%) በሁለተኛ ምርጫቸው፣ 388 (29.5%) በደልዳይ ኮሚቴ የተመደቡ ሲሆን 8 ሰራተኞች ግን ምደባ ያላገኙ የነበሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ምደባ እንዲያገኙ ስለተደረገ ያልተመደቡት ሰራተኞች ቁጥር ወደ 6 እንዲወርድ ተደርጓል። በአጠቃላይ በመዋቅሩ መሰረት የድልድል ስራ የማከናወን ሂደቱ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ክንውን ነው የነበረው።

ሰንጠረዥ 7. በአዲሱ መዋቅር መሰረት የተደረገ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ድልድል

| ተ.ቁ. | አይነት | ዋና ግቢ | | | ምውፃእ ወርቂ ግቢ | | | የተጠቃለለ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | መቶኛ |
| 1 | ለውድድር ያመለከቱ | | | | | | | 408 | 909 | 1317 | 100 |
| 2 | በ1ኛ ምርጫቸው የተመደቡ | 196 | 234 | 430 | 36 | 71 | 107 | 231 | 306 | 537 | 40.77 |
| 3 | በ2ኛ ምርጫቸው የተመደቡ | 73 | 213 | 286 | 15 | 73 | 88 | 88 | 286 | 374 | 28.40 |
| 4 | በኮሚቴ የተመደቡ | 62 | 219 | 281 | 17 | 90 | 107 | 79 | 309 | 388 | 29.46 |
| 5 | በሂደት ያቋረጡ | | | | | | | 3 | 7 | 10 | 0.76 |
| 6 | ምደባ ያላገኙ | 6 | 2 | 8 | | | | 6 | 2 | 8 | 0.61 |
| ድምር | | 337 | 668 | 1005 | 68 | 234 | 302 | 407 | 910 | 1317 | 100.00 |

በመመርያው መሰረት ምደባው ከተጠናቀቀ በኋላ ቅሬታ ያላቸው ሰራተኞች ቅሬታቸውን ወደ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እንዳለባቸው ስለሚታወቅ 298 ሰራተኞች ቅሬታቸውን ለኮሚቴው አቅርበው የኮሚቴው ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

## 11.ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

በበጀት አመቱ በርካታ ስራዎች የተሰሩ መሆናቸው ከሪፖርቱ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በርካታ ችግሮችና ፈተኛዎች ያጋጠሙ መሆናቸው ደግሞ ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል። በዚሁም መሰረት በአመቱ ያጋጠሙት ዋና ዋናዎቹ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፤

11.1. የበጀት እጥረት ባጠቃላይ በተለይም ደግሞ የተማሪዎች ምግብ በጀት እጅግ አነስተኛ መሆን። ለአመቱ የተመደበልን በጀት በክፍል 9 የተብራራ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ለመስራት ከሚያስበው (በተለይም ዩኒቨርሲቲው ከደረሰበት ውድመትና ጉዳት አንፃር) በጣም አነስተኛ ነው። ዩኒቨርሲቲው በርካታ የግንባታ ስራዎች ያሉት ሲሆን በዚሁ በጀት እነዚህን ስራዎች ማከናወን አስቸጋሪ ነው። ከበጀት እጥረት ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ሌላው ጉዳይ መላው የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች የ2014 ውዝፍ ደመወዛቸው ያልተከፈላቸው መሆኑ ነው። ችግሩን ለመፍታት ተደጋጋሚ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም ሊፈታ ያልቻለ ችግር ሆኖ ቀጥሏል። የተማሪዎች ምግብን አስመልክቶ ለአንድ ተማሪ በቀን የተመደበው በጀት 22 ብር ስለሆነ በዚህ ገንዘብ

አንድን ተማሪ መመገብ ፈፅሞ የማይቻል ስለሆነ ከሌሎች የበጀት መስመሮች በመውሰድ ነው የምግብ በምግብ ወጪውን ለመሸፈን የተሞከረው። በአመቱ በአማካይ የአንድ ተማሪ የምግብ ወጪ 100.90 እንደነበረ ነው የተሰላው። ስለዚህ ይህ መጠን በ2017 እንዲስተካከል ካልተደረገ ችግሩ የከፋ እንደሚሆን ከወዲሁ መተንበይ አያስቸግርም።

11.2. ከመውጫ ፈተና ጋር ተያይዘው የሚነሱ የተማሪዎች ጥያቄዎች፤ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና መውሰድ እንዳለባቸው መመርያው ያስገድዳል። በመመርያው መሰረት ከነሐሴ 2014 በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ወስደው ካላለፉ የዲግሪ ሰርቲፊኬት ሊሰጣቸው አይችልም። ሆኖም ግን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአመቱ በርካታና አሰልቺ ጥያቄዎች ከተማሪዎች ሲነሱ ተስተውለዋል። ጥያቄዎቹ ዘርፈ ብዙ ሲሆኑ በዋናነት ግን፤ (1) ከ2014 በፊት መመረቅ የነበረባቸው ነገር ግን በኮቪድ እና በጦርነቱ ምክንያት ትምህርት እንዲያቆሙ የተገደዱት ይህ የመውጫ ፈተና እኛን ሊመለከት አይገባም የሚል ጥያቄ አመቱን ሙሉ ያስቸገረ ጥያቄ ሆኖ ነው ያለፈው፣ (2) ዩኒቨርሲቲው ተዘግቶ በነበረበት ጊዜ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች እንዲማሩ እድል የተሰጣቸው እና በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ከነሐሴ 2014 በፊት አጠናቀናል ብለው የሚያምኑ እኛ ጋር ያለው ሪኮርዳቸው ሲታይ ያልወሰዱት ወይም ያላለፉበት/ባቸው ኮርስ/ኮርሶች ስለሚገኙ እኛ ጋር መጥተው የጎደላቸውን መውሰድ ስላለባቸው እና እነዚህን አሟልተው የሚያጠናቅቁበት ጊዜ ደግሞ በ2016 ስለሚሆን ኮርሶቹን ከሚሟላቱ አልፎ የመውጫ ፈተና መውሰድ የሚጠበቅባቸው ሲሆን እኛን አይመለከትም የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ። ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ጊዚያዊ ሰርቲፊኬት የሰጣቸውና በስራ ላይ ተቀጥረው የሚገኙ መሆናቸው ጉዳዩን ያወሳስበዋል። ለማንኛውም እነዚህ ጥያቄዎች ሲነሱ ተማሪዎቹን የመውጫ ፈተና መውሰድ እንዳለባቸው በዩኒቨርሲቲው የሚነገራቸው ቢሆንም ፈቃደኝነቱ ስለሚጉድላቸው ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሄደው የሚያመለክቱም ብዙ ናቸው። ከትምህርት ሚኒስቴርም አቅጣጫ ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ይመስላል።

11.3. የላቦራቶሪና ዎርክሾፕ አገልግሎቶች በተገቢው መንገድ መጀመር አለመቻላቸው፤ የተበላሹና የወደሙ የላቦራቶሪና የዎርክሾፕ መሳርያዎችን አስመልክቶ የሚጠገኑትን ለመጠገን የሚተኩትን ገዝቶ ለመተካት ጊዜ የሚፈልግ ጉዳይ ሆኖ ስለተገኘ በአመቱ ሊሰራ አልቻለም። አንዳንዶቹ የላቦራቶሪ ክፍሎች ደግሞ በጦር መሳርያ በቀጥታ ጉዳት

የደረሰባቸው በመሆኑ የጥገና ስራም ይጠይቃሉ። እነዚህን የመጠገንና የመተካት ስራ በ2017 ትኩረት ተስጥቶት የሚሰራ ሲሆን ከወዲሁ የተጀማመሩ ስራዎችም አሉ።

11.4. የውሃ አገልግሎትን ጨምሮ የመብራት እና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሰጡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ትራንስፎርመሮች የተቃጠሉ በመሆናቸው እነሱን ለመጠገን ወይም በአዲስ ለመተካት ሌላው ያጋጠመ የአመቱ ፈተና ነበር። ብዙ ሙከራዎች የተደረጉ ቢሆንም ትራንስፎርመሮቹን ለመጠገን ይሁን አዲስ ለመተካት የተሳካ ስራ ሊሰራ አልተቻለም። በ2017 የበጀት አመት የተሳካ ስራ ይሰራል ተብሎ ይጠበቃል።

11.5. ከፍተኛ የመኪኖች እጥረት፤ ዩኒቨርሲቲው ከነበሩት መኪኖች ውስጥ ብዛት ያላቸው ስለተዘረፉ ከፍተኛ የመኪና እጥረት ስላጋጠመው በእለታዊ ስራዎቹ ላይ ያጋጠመው ችግርና መጉላላት እጅግ አስቸጋሪ ነው የነበረው። እንዲህ መቀጠሉ አስቸጋሪ ስለሚሆን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት (ለምሳሌ ገንዘብ ሚኒስቴር) ከፍተኛ ድጋፍ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

11.6. የተማሪዎች ውጤት በወቅቱ አለመግባት፤ የተማሪዎች ውጤት በወቅቱ ወደ ሲስተሙ (Student Management Information Systems SIMS) አለመግባት ሌላው በአመቱ ያጋጠመ ችግር ነው የነበረው። በዚሁም ምክንያት ተማሪዎች የሚገኙበት የትምህርት ሁኔታ (Academic Status) እንዲሁም የመረጃ አያያዝ (ለምሳሌ በሬጂስትራር እና በተማሪዎች ዲን) ላይ ወጥነት አለመኖር ችግር አስከትሏል። ይህ ጉዳይ የዲኖችና የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ትኩረት የሚሻ ነገር ነው።

እዝል 1፣ ዩኒቨርሲቲው ከተመሰረተበት ጀምሮ እስከ ሰኔ 2016 ድረስ ያስመረቃቸው ተማሪዎች መረጃ

| Graduation Year (E.C) | Program | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Under graduate | | | | | | | | | | | | Post graduate | | | | | | | | | Grand total | | |
| | Regular | | | extension | | | summer | | | S. total | | | regular | | | extension | | | S. total | | | | | |
| | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| 2006 | 128 | 220 | 348 | | | | | | | 128 | 220 | 348 | | | | | | | | | | 128 | 220 | 348 |
| 2007 | 652 | 402 | 1054 | | | | 214 | 102 | 316 | 866 | 504 | 1370 | | | | | | | | | | 866 | 504 | 1370 |
| 2008 | 1275 | 939 | 2214 | 60 | 22 | 82 | 276 | 114 | 390 | 1611 | 1075 | 2686 | | | | | | | | | | 1611 | 1075 | 2686 |
| 2009 | 1481 | 1002 | 2483 | 69 | 37 | 106 | 378 | 139 | 517 | 1928 | 1178 | 3106 | | | | | | | | | | 1928 | 1178 | 3106 |
| 2010 | 2017 | 1166 | 3183 | 150 | 110 | 260 | 805 | 258 | 1063 | 2972 | 1534 | 4506 | 37 | 23 | 60 | 19 | 2 | 21 | 56 | 25 | 81 | 3028 | 1559 | 4587 |
| 2011 | 2161 | 1411 | 3572 | 152 | 82 | 234 | 964 | 308 | 1272 | 3277 | 1801 | 5078 | 45 | 14 | 59 | 48 | 12 | 60 | 93 | 26 | 119 | 3370 | 1827 | 5197 |
| 2012 | 145 | 108 | 253 | 95 | 79 | 174 | 1062 | 383 | 1445 | 1302 | 570 | 1872 | 14 | 4 | 18 | 8 | 1 | 9 | 22 | 5 | 27 | 1324 | 575 | 1899 |
| 2013 | 1875 | 979 | 2854 | 27 | 10 | 37 | | | 0 | 1902 | 989 | 2891 | 25 | 2 | 27 | 32 | 4 | 36 | 57 | 6 | 63 | 1959 | 995 | 2954 |
| 2014 | 1351 | 749 | 2100 | 58 | 78 | 136 | 37 | 20 | 57 | 1446 | 847 | 2293 | 4 | 0 | 4 | | | 0 | 4 | 0 | 4 | 1450 | 847 | 2297 |
| 2015 | 79 | 33 | 112 | | | | | | | 79 | 33 | 112 | | | | | | | | | | 79 | 33 | 112 |
| 2016 | 658 | 212 | 870 | 43 | 19 | 62 | | | | 701 | 231 | 932 | 42 | 13 | 55 | 101 | 17 | 118 | 143 | 30 | 173 | 844 | 261 | 1105 |
| Total | 11822 | 7221 | 19043 | 654 | 437 | 1091 | 3736 | 1324 | 5060 | 16212 | 8982 | 25194 | 167 | 56 | 223 | 208 | 36 | 244 | 375 | 92 | 467 | 16587 | 9074 | 25661 |

ማስታወሻ፣ በ2016 ምረቃቸው ከፀደቀላቸው ውስጥ ቀደም ብለው መመረቅ የነበረባቸው ስለነበሩ በዚሁ መሰረት እንዲስተካከል የተደረገ ነው። በክፍል 2 ሰንጠረዥ 1 ከተመለከተው የ2016 ተመራቂዎች ብዛት ጋር የሚታየው ልዩነት በዚህ ምክንያት መሆኑ ማስታወሱ ተገቢ ነው።

### እዝል 2፤ በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት የሚከናወኑ መካከለኛ (Medium) የምርምር ፕሮጀክቶች

| S.No. | College | Host Department | Title of Project Proposal | Approved budget |
|---|---|---|---|---|
| 1 | CET | Mechanical | Design and manufacturing of versatile and flexible patient bed | 168,000 |
| 2 | CET | Mechanical | Design development and Manufacturing Manually Operated Hand Rope Piston Water Pump: Case study of Tigray | 168,000 |
| 3 | CET | Mechanical | Design and development of Small-scale community based solar powered Irrigation System to Enhance food security in Tigray Region as a sustainable Solution for Postwar Rehablitation: The cas of Agulae Irrigation farm | 168,000 |
| 4 | CET | Mechanical | Design and development of mobility equipment for students with physical disability in a classroom | 168,000 |
| 5 | CET | Chemical | Waste management and recycling: Design and manufacturing of Aluminum recycling waste fuel gas furnace for structural applications. The case study of sampled cities in Tigray Region. | 168,000 |
| 6 | CET | Chemical | Production, Characterization and Process Optimization of Biogas from a mixture of Animal Manure and Food Wastes using a Prototype Anaerobic Digeste | 168,000 |
| 7 | CET | chemical | Development and Evaluation of Optimized Complementary Foods Produced from maize, soybean and chickpea | 168,000 |
| 8 | CET | Chemical | EXPERIMENTAL INVESTIGATION ON BLENDED FIBER REINFORCED HIGH STRENGTH CONCRETE | 168,000 |
| 9 | CET | Comp. Sc. | Digitial Research and Community Service Data Management System | 100,000.00 |
| 10 | CNCS | Biology | Post-war investigation on the population status and habitat of geladas (theropithecus gelada unknown subspecies) in the escarpments of eastern tigray, ethiopia: implication for ecotourism promotion | 200,000.00 |
| 11 | CNCS | Geology | Evaluation of the water supply system and digitalized database generation toward its rehabilitation in towns categorized as “cluster 2”, eastern zone, tigray, ethiopia | 199,547.25 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 12 | CNCS | Chemistry | An integrated approach to sustainable management and remediation of hazardous chemical wastes: implication to rehabilitate war-scarred laboratories in eastern tigray zone, northern Ethiopia | 199,983.00 |
| 13 | CNCS | Chemistry | Production and characterization of vermicompost made from locally available organic waste materials | 199,350 |
| 14 | CMHS | Medical Laboratory | Soil-Transmitted Helminthiasis and associated malnutrition among school age children of war affected areas of Tigray, Ethiopia, 2024-2026 | 199,900.00 |
| 15 | CMHS | Reproductive and family health | Determinants of involvement Decision in community-based health insurance membership among households of Gantaafeshum woreda, Eastern zone, Tigray, Ethiopia, 2024: Mixed Study | 200,000.00 |
| 16 | CMHS | Nursing | Effect of Community Health Education and Food Demonstration on Infant and Young Child Feeding Practice among Mothers of Hahayle Woreda, North Ethiopia, Quasi Experimental Study, 2024 | 199,802 |
| 17 | CMHS | Reproductive and Family Health | Effect of community-based pregnancy test service on improving timely access to antenatal care in rural districts of Eastern zone, Tigrai, Ethiopia: A quasi-experimental study design | 199,996 |
| 18 | CMHS | Reproductive Health | Effectiveness of Trauma-Focused Cognitive Behavioral Therapy (TF-CBT) on Post-Traumatic Stress Disorder and Depression among War-Affected Secondary School Adolescents in Adigrat, Eastern Zone of Tigray, Ethiopia, 2024. | 199,771.00 |
| 19 | CAES | Horticulture | Effects of a Climate-Smart Push-Pull Technology on Pest Management, Soil Fertility Improvement and Fodder Production in a Maize-Potato Intercropping System | 199526.26 |
| 20 | CAES | Plant Science | Crop Genetic Wipeout and Seed Disaster in Tigray, northern Ethiopia | 200000 |
| 21 | CAES | Natural Resources Management | Climate smart agriculture: prioritization and adoption strategies by rural livelihoods and their impact on agricultural production across agro-ecologically varied farming systems, a case study from drought prone areas in eastern Tigray, northern Ethiopia | 200000 |
| 22 | CAES | Plant Science | Morphological and nutritional variations among barley (Hordeum vulgare L.) accessions and evaluation of the impact of Tigray war on the seed system and soil characteristics in Eastern Tigray Zone, Ethiopia | 199977.75 |
| 23 | CBE | Management | Assessing the Role of Entrepreneurship Development in Post Conflict Context; Implication for Post War Reconstruction Program of Tigray | 200,000.00 |
| 24 | CBE | Tourism management | Strategic Responses for Post War Tourism Recovery in Eastern Tigray: Domestic Tourism as Strategic Tool | 199,314.00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 25 | CBE | Management | Challenges and Emerging Trends of the Broken Promises of SDGs in Tigrai, (Evidence from Eastern Zone of Tigrai Regional State of Ethiopia) | 200,000.00 |
| 26 | CBE | Management | Interventions and settings in the livelihood of IDPs as a prospect of post-war recovery: A Case of Adigrat IDP Centers. | 199,950 |
| 27 | CSSH | English Language and Language | Damage Assessment and Revitalization of Cultural Heritages in Eastern Tigray: Addressing Aftermath of the Devastating War in Kilte Awla'elo and Ganta Afeshum Woredas | 200,000 |
| 28 | CSSH | Geography and Environmental study | Responsiveness of Tigray's higher education system to the needs of post-war reconstruction and development: Opportunities, Practices and Challenges | 200,000 |
| 29 | CSSH | Civics and ethical studies | Rebuilding Amidst Aftershocks: Upholding Human Rights and Safeguarding Internally Displaced Persons Protection in Post-War Tigra | 198,468 |
| 30 | CSSH | Geography and Environmental study | Examining Post War Food Insecurity Rehabilitation, in Eastern Zone of Tigray Regional State, Ethiopia | 199,924 |
| 31 | SL | Law | Addressing the rights and needs of conflict-induced IDPs in post Tigray War: looking for durable solution: The case of Eastern zone | 199,998 |
| 32 | SL | Law | Post war prevalence of crimes: Causes, Challenges and the way forward the case of Tigray | 199,990 |
| 33 | Beles I | Beles Institute | Development of Avocado seed kernel starch-Based edible coating for enhancing the postharvest quality and shelf-life of cactus fruit. | 200000.00 |
| 34 | Beles I. | Beles Institute | Evaluation of the resistance of cactus pear populations to Carmine Cochineal in Tigray, Northern Ethiopia | 200000.00 |
| Total | | | | 6439497.26 |